ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

# የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ

(በሠኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ታረቀኝ አይሶ

ሐምሌ 2013

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ

( በሠኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት )


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር


ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ሟሟያ ቀረበ ጥናት


በ

ታረቀኝ አይሶ

አማካሪዎች

ምህረት ሳዳሞ ( ዶ/ር )

ለማ ንጋቱ ( ዶ/ር )



ሐምሌ 2013

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ
# የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ
# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
# የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

“የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ” (በሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)፤ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በታረቀኝ አይሶ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራት እና የወጥነት  መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

<u>**የፈተና ቦርድ አባላት**</u>

አማካሪ -------------------------- ፊርማ-----------------------ቀን----------------------------

የውጭ ፈታኝ -------------------ፊርማ-----------------------ቀን ----------------------------

የውስጥ ፈታኝ--------------------ፊርማ---------------------ቀን------------------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ረቂቁን በማረም፣ ማስተካከያ በመስጠት፣ ድጋፍቸው ላልተለየኝ አማካሪዎቼ ዶክተር ምህረት ሳዳሞ እና ለዶክተር ለማ ንጋቱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል የትምህርቴንና የመመረቂያ ጽሁፌን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን ወጪ በመጋራት እገዛ ላደረገልኝ ለዉድ ወንድሜ መሠረት ተረፈ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሰዉ፡፡

በማስከተልም ለጥናቱ መሳካት መረጃዎችን በማሰባሰብ የረዱኝንና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በቀናነት በመርዳት ለተባበረኝ ለሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መንግስቱ መኮንን እንዲሁም ዉድ ጊዜያቸዉን ሰዉተዉ ፈተና በማረምና የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለረዱኝ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ በጥናቱ ለተሳተፉት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለትብብራችሁ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

በመጨረሻም በትምህርት ቆይታዬ የሞራል ድጋፋችሁ ላልተለየኝ ዉድ ቤተሰቦቼ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ "የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ነዉ፡፡" ይህን ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ ሙከራዊ የምርምር ስልት የተከተለ ሲሆን፤ ለጥናቱ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመች ናሙና ተመርጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ 9 የአስረኛ ክፍል መማሪያ ሲኖረዉ፤ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች በቀላል ዕጣ ናሙና ተመርጧል፡፡ በመማሪያ ክፍሎቹ 120 ተማሪዎች ሲገኙበት፤ ለቁጥጥርና ለሙከራ ቡድን ለመመደብ የችሎታ ደረጃቸዉን ለማወቅ የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በፈተናዉ ተቀራራቢ ዉጤት ያመጡትን 50 ተማሪዎች በመዉሰድ በተራ የዕጣ ናሙና ስልት አንደኛዉን ለሙከራ ቡድን ሌላኛዉ ለቁጥጥር ቡድን ዉለዋል፡፡ የቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ዉጤት 27.426 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 27.466 ነዉ፡፡ የp ዋጋዉ 0.960 ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ የጉልህነት ደረጃዉን ($p<0.05$) የበለጠ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከቅድመ ትምህርት ፈተና በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ ቀድሞ ሲማሩበት በነበረዉ ለሙከራ ቡድኑ ክሂሎቹን በማቀናጀት ለተከታታይ አራት ሳምንታት ትምህርቱን በማስተማር የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት ዉጤትም በአማካይ የሙከራ ቡድኑ 40.333 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 32.293 ነዉ፡፡ የp ዋጋ .000 ሆኖ ከጉልህነት ደረጃዉ ($p<0.05$) ያነሰ ነዉ፡፡ በዚህም በክሂሎቹ ቅንጅታዊ አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መሻሻል የታየ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለዉ ፈተና ሲሆን፤ መረጃን ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋለዉ መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ነዉ፡፡ በጥናቱ የተደረሰበት መደምደሚያ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ማሻሻል እንደቻለ ከተገኘዉ የዉጤት ንጽጽር ማወቅ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም እነዚህን ክሂሎች ይበልጥ ለማዳበር የትምህርት ቤቱ የስነ-ጽሑፍ፣ የድራማ፣ የሚኒ ሚዲያ ክበብ ተጠሪዎች ተማሪዎችን በነዚህ ክበባት እንዲመዘገቡ ቢያደርጉና የተዘመገቡ አባላትም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከተለያዩ መጽሐፍትና መጽሔቶች አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ አጠናቅረዉ በየጊዜው በሰንደቅ ዓላማ፣ በዕረፍት ጊዜያቸው በንባብ እንዲያቀርቡ ቢያደርጉ፤ የሚል አስተያየት አጥኚዉ ሰጥቷል፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........................................ i
አጠቃሎ........................................ ii
ማውጫ ........................................ i
ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................ 3
1.3. የጥናቱ መላምት ........................................ 4
1.4.የጥናቱ አላማ........................................ 4
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 5
1.6. የጥናቱ ወሰን ........................................ 5
1.7. የጥናቱ ውስንነት........................................ 6
1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ ........................................ 7
ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት........................................ 8
2.1.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........................................ 8
2.1.1. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት ........................................ 8
2.1.2.የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች........................................ 9
2.1.3. የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ ........................................ 10
2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት ........................................ 11
2.2.1. የአንብቦ መረዳት ስልቶች........................................ 13
2.2.2. የጥሩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄ ባህሪያት ........................................ 14
2.3. የጽህፈት ክሂል ምንነት........................................ 15
2.3.1. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ ........................................ 16
2.4. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር ........................................ 17
2.4.1. የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍን ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ ጠቀሜታ ....... 18
2.4.2. የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች ............... 19
2.5. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................ 23

ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና አካሄድ ........ 25
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 25
3.2. የጥናቱ አካሄድ ........ 25
3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 25
3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 26
3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 26
3.3.3. የተማሪዎች አመራረጥ ........ 26
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 27
3.4.1. ፈተና ........ 27
3.5. የማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት ........ 29
3.6. ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች ........ 30
3.7. የመረጃ  አተናተን ዘዴ ........ 30
ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ወጤት ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........ 32
4.1. የጥናቱ ዉጤት ትንተና ........ 32
4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 41
ምዕራፍ አምስት፤ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........ 44
5.1.ማጠቃለያ ........ 44
5.2. መደምደሚያ ........ 45
5.3. አስተያየት ........ 46
ዋቢ ጽሑፎች ........ 47
አባሪዎች ........ 50

## የሰንጠረዥ ማውጫ ገፅ

ሠንጠረዥ1. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታተስቲክስ………………………………………………………………… 32

ሰንጠረዥ 2. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት……………………………………………………………….… 33

ሰንጠረዥ3. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ………………………………………………. 34

ሠንጠረዥ 4. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ- ቴስት…………………………………..… 35

ሠንጠረዥ 5. የሙከራዉ ቡድን የቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ…………………………………………………………..….. 36

ሠንጠረዥ6. የሙከራዉ ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና  አማካይ ዉጤት ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ- ቴስት………………… 37

ሠንጠረዥ 7. የቁጥጥር  ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ………………………...….. 38

ሠንጠረዥ 8. የቁጥጥር ቡድን ቅድመ-ትምህርትና ድህረ -ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር  በዳግም ልኬታ  ናሙናዎች ቲ- ቴስት…………..…… 39

ሠንጠረዝ 9. የመላምት ፍተሻ ዉጤት (two tailed) የt- ቴስት ስሌት..……………………………..… 40

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ከሚቀረጽባቸዉ ዐበይት ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ለማዳበር ሲሆን በተጓዳኝ የሰዋሰዉንና የሥነ-ጽሑፍ መሠረታዊ ዕዉቀት በማስጨበጥ በቋንቋዉ ጥሩ አንባቢና ጥሩ ጸሐፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነዉ፡፡ አለምና ጽጌ (1997) እንደሚገልጹት የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች "የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማጎልበት እንዲሁም ተጓዳኝ የቋንቋ ክሂሎች የሆኑትን የሰዋሰዉና የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊ ዕዉቀቶችን ለማዳበር ነዉ::" እነዚም ክሂሎች በክፍል ዉስጥ እንዴት መተግበር እንዳለባቸዉ መርሀ ትምህርት ተዘጋጅቶላቸዉ በተናጠልና በቅንጅት ይሰጣሉ፡፡ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው (Gilbert 1982)::

Atkins (1996) ክሂሎችን አጣምሮ ማስተማር ማለት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች የተወሰኑትን አጣምሮ የማስተማር አቀራረብና ክንዉንን ይመለከታል፡፡ በአንድ የቋንቋ ትምህርት አንድን ክሂል ከጽህፈት ወይም ከንባብ ጋር አጣምሮ ሲያቀርብ የተቀናጀ አቀራረብ ይባላል፡፡ በመሆኑም በዕለት ተዕለት ተግባቦት መስተጋብር ስንጽፍ እናነባለን፤ ስንናገር እናዳምጣለን፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ የክሂሎች ግኑኝነት ሁኔታ በክፍል ዉስጥም በበለጠ ማጠናከርና መተግበር ስንችል ነዉ የተዋሀደ የቋንቋ ክሂል ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ አደረግን ማለት የምንችለዉ፡፡ ቅንጅታዊ የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ላይ በአራት የቋንቋ ክሂሎች ዙሪያ ዉጤታማ የመማር የማስተማር ሁኔታን እና ትርጉም ያለዉ የመማር አዉድን ይፈጥራል ይላሉ፡፡

ቋንቋን ለማስተማር ሲታቀድ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ስልቶች አብረዉ ይነሳሉ፡፡ ይህም እንደ ትምህርቱ አላማ ግብ እንዲሁም በየዘመኑ እንደነበረዉ የቋንቋ ፍልስፍና መሠረት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን ሲነደፉ ይታያል፡፡ ከነዚህም መካከል ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገዉ ሁኔታ ግብ እንዲመታ ያግዛል ተብሎ ከሚጠቀሱት አቀራቦች ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ክሂል ይበልጥ እንዲያጎለብቱ ለማድረግ በጥንቃቄ የታቀደ የቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በአግባቡ ለማስተማር የሚያስችል ስልት መርጦ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል (Little wood 1981)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረጹት ዓበይት ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበርና ማጎልበት ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን (Byrne 1981) ገልጸዋል፡፡ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተዉ ምሁራን የሚከተለዉን ብለዋል፡፡

Byrne (1981) እና Mc Donugh and Show (1992) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ወቅት አንዱ ክሂል ሲነሳ ሌላዉ ተከትሎ የሚነሳ በመሆኑ ተያያዥነት ያላቸዉን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ማስተማርን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳዉ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ዉስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረዉ እንዲነሱ በማድረግ እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ ነዉ፡፡ የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸዉ ዓላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር ነዉ፡፡ ይህ ዓላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለዉ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በተገቢዉ መንገድ ተቀናጅተዉ በክፍል ዉስጥ ሲማሩ ነዉ ( Bill 1996)::
ሞገስ (1999) ባደረጉት ጥናት Beerd gew (2003) ዋቢ አድርገዉ እንደገለጹት በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ማንበብና መጻፍ እንደተለያዩ አላባዊያን ተደርገዉ ይወሰዱ ነበር፡፡ በዚህም በማንበብና በመጻፍ ትስስር ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የተለመደ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም በ1970ዎቹ ዓመታት ላይ ግን በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለዉ ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምርምሮቹ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክሂሎች መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

Rudel (1997) እንደገለጹት በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር መኖሩንና በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የተሻለ ዘዴ ነዉ የሚባለዉ ቅንጅታዊ አቀራረብ ሲሆን የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገዉ ደረጃ ግቡን እንዲመታ ያግዛሉ ተብለዉ ከሚጠቀሱት ዉስጥ አንዱ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ነዉ Little Wood (1981)፡፡

Block (1997) የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ዐብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና የተረዱትን ጽሁፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የሚያስችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ መተንበይና መገመት በጥልቀት ማሰብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ የቀረቡትን የምሁራኑን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የዚህ ጥናት አቅራቢ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ለማስተማር ይረዳሉ የተባሉትን ዘዴዎች በመተግበር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለዉን ዉጤታማነት በጥናት ለመፈተሽ አቅዶ ይተገብራል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ቋንቋን በማስተማር ሂደት ትኩረት የሚሰጠዉና በዋናነት የሚጠቀሰዉ የቋንቋ ክሂሎችን ማስተማር ነዉ፡፡ የቋንቋ ክሂሎች የሚባሉትም ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ናቸዉ፡፡ ከነዚህ አራቱ ክሂሎች መካከል ማንበብና መጻፍ በትምህርት የሚገኝና የሚዳብር መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ የቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ አንዱን ክሂል ብቻ ነጥለዉ ማስተማር የማይቻል በመሆኑ አንዱን ክሂል ሲያስተምሩ በተዘዋዋሪ ሌላኛዉን ክሂል ማስተማራቸዉ የማይቀር ነዉ፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ክሂሎች በባህሪያቸዉ እርስ በርስ የሚደጋገፉና የአንዱ ክሂል መዳበር ለሌላኛዉ ክሂል መዳበር የየራሳቸዉ አስተዋጽዖ አላቸዉ፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም በተለያዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለአስር ዓመታት ያህል በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስተምሯል፡፡ ባስተማራቸዉ ጊዜያቶች ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፋቸዉ ላይ ያለዉን ምንባብ እንዲያነቡና የተረዱትን ሀሳብ አቀናብረዉ፣ አሳጥረዉ በጽሁፍ እንዲመልሱ በሚደረግበት ጊዜ ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብቦ የመረዳትና የምንባቡን የሀሳብ ፍሰት ጠብቀዉ አቀናብረዉ በጽሁፍ የመመለስ ዉስንነት እንዳለባቸዉ አጥኚዉ በዉል ተገንዝቧል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የወሰደዉ አንደኛ የመርሀ ትምህርት ቀራጮች ክሂሎቹን ይበልጥ ለማዳበር በሚረዳ መልኩ ባለማዘጋጀታቸዉ ይሆን፣ ሁለተኛ የመጽሐፍ አዘጋጆች ሁለቱን ክሂሎች በቅንጅት ለማስተማር የመማሪያ መጽሐፉን ምቹ ባለማድረጋቸዉ ይሆን የሚል ሀሳብ ቢያድርበትም፣ አጥኚዉ ይበልጥ እንደ ምክንያት የወሰደዉ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚረዳ ማቀናጃ ዘዴ በግልጽ ባለመቀመጡ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በመሆኑም ክሂሎቹን ይበልጥ ለማዳበር ይረዳሉ ተብለዉ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን የክሂሎች ማቀናጃ ብልሃቶችን በተግባር ላይ በማዋል የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለዉን አስተዋጽዖ ለማየት አጥኚዉ ትኩረቱን በክሂሎቹ ላይ በማድረግ ለጥናቱ በተመረጡት ተማሪዎች ላይ የሚያመጣዉን የዉጤት ለዉጥ በከፊል ሙከራዊ ጥናት በማረጋገጥ ዘዴዉ ዉጤታማ የሚሆን ከሆነ ከዚህ በኋላ መምህራን በዚህ መልኩ ትኩረት ሰጥተዉ ክሂሎቹን አቀናጅተዉ እንዲያስተምሩ ለማድረግ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ በትምህርት ቤት፣ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች አጠቃላይ በዕዉኑ ዓለም ላይ ያለዉ አስተዋጽዖ ከፍተኛ በመሆኑ አጥኚዉ በጥናት ለማረጋገጥ ተነሳስቷል፡፡

## 1.3. የጥናቱ መላምት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን መላምቶችን ይዟል፡፡

1. የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በተጠኚ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ልዩነት ይኖራል ፡፡
   ( አማራጭ መላምት )
2. አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በተጠኚ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ  መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ልዩነት አያመጣም፡፡
   ( አልቦ መላምት )   የሚሉትን ሁለት መላምቶች ይዟል፡፡

## 1.4.የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ነዉ፡፡

በዚህ አጠቃላይ ዓላማ ስርም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ፋይዳ  መፈተሽ፤
2. አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል በቅንጅት ማስተማር በተጠኚ ተማሪዎች መካከል ሊያመጣ የሚችለዉን  የችሎታ ልዩነት መመርመር፤

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ እንደሆነ ቀደም ብሎ በዓላማው ላይ ተገልጿል፡፡ የጥናቱን ዉጤት መሠረት በማድረግ  የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- **ለተማሪዎች፡-**
  - ✓ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ በቀላሉ እንዲያጎለብቱ እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡
  - ✓ የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታቸዉን በማዳበር በስራና በትምህርት ገበታቸዉ ያለ አንዳች ችግር ተጠቃሚ ሊያደርጋቸዉ ይችላል፡፡
- **ለመምህራን፡-**
  - ✓ የጥናቱ ዉጤት መሠረት በማድረግ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የሚሰጠዉን አዎንታዊ ፋይዳ በመረዳት ክሂሎችን አቀናጅተዉ እንዲያስተምሩ ይገፋፋል፡፡
- **ለጥናት አድራጊዎች፡-**
  - ✓ ወደ ፊት ይህን መሰል ርዕሰ ጉዳይ ላይ  ጥናት ለሚያደርጉ አጥኝዎች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ትኩረት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ ከሚገኙት ስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነዉ፡፡ በዚህ ምርምር ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መሸፈን በሂደቱም የሚገኙትን መረጃዎች ለመቆጣጠር አዳጋች ስለሚሆንና አጥኚዉም በትምህርት ቤቱ በመምህርነት እያገለገለ ያለ ስለሆነ ከስድስቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺ ንሞና አወሳሰድ ዘዴ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡

ሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ደረጃ የሚማሩ ዘጠኝ ክፍሎች (section) ሲኖሩ እነዚህን ክፍሎች በሙሉ ከጊዜ፣ ከሰው ኃይልና ገንዘብ አንፃር በመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሳ በጥናቱ ለመሸፈን አዳጋች በመሆኑ ነዉ፡፡ ከዚህ ሌላ ጥናቱ የአንብቦ መረዳትን ክሂል

ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ ብቻ ያተኩራል ሌሎች ቀሪ ክሂሎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት ውሰጥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ጥናቱን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወንና ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ነገሮች ሁሉ ለማካተት ጥናቱ ውስን የሚሆንባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም፡-

አንደኛ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ነዉ፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የተማሩባቸው የማስተማሪያ ስልቶች በተቃራኒ ፈረቃቸዉ የተከናወነ ቢሆንም፣ ከትምህርት ጊዜያቸዉ ዉጪ ተገናኝተዉ ሊወያዩበት ሲለሚችሉና ከማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ ዉጭ መቆጣጠር ስለማይቻል በጥናቱ ዉጤት ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮ ሊሆን ይችላል፡፡

ሁለተኛ በአስረኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት እንዲያሻሽሉ ተብሎ ከተደራጁ ይዘቶች ውስጥ አንዱ የአንብቦ የመረዳትና  የመጻፍ ክሂል ነዉ፡፡ በዚህ ክሂል ውስጥ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል የሚያዳብሩ የተለያዩ ይዘቶች እየጻፉ እንዲለማመዱ መማሪያ መጽሐፍት መመሪያ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን መመሪያዎቹ ክሂሎቹን ለየብቻ እንጂ በቅንጅት እንድማሩ የሚጋብዙ አይደለም፡፡ ከዚህም አንጻር ውስንነት ይኖረዋል፡፡

## 1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

- **ቅንጅታዊ አቀራረብ:-** በአንድ ክፍለ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማቀናጀት አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ የሚደረግበት ዘዴ ነው ( Byren 1981)፡፡
- **አንብቦ የመረዳት ክሂል:-** የአንድን ጽሁፍ መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው (Green wood 1981)፡፡
- **የመጻፍ ክሂል፡-** መጻፍ የሀሳብ አቀነባባርን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ የቃላት አመራረጥ እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው ( Byren 1988)፡፡
- **መላምት**፡- አንድ ምርምር ከተካሄደ በኋላ ሊረጋገጥ የሚችል ወይም ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ውጤት ነው፡፡ የሙከራ ቡድን የአንብቦ መረዳትና ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት የተማሩትን የመለክታል፡፡
- **የቁጥጥር በድን፡-** አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ከ2004 ዓመት መማሪያ መጽሐፍ የሚከተለው መደበኛው የትምህርት አሰጣጥ የተማሩትን ይመለክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች

ይህ ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበትን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች የሚዳሰስበት ነው፡፡

በዚህም መሰረት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት፣ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች፣ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ፣ የአንብቦ መረዳት ምንነት፣ የአንብቦ መረዳት ስልቶች፣ የጽህፈት ክሂል ምንነት፣ የጽህፈት ትምህርት አላማ፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር፣ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ ጠቀሜታ፣ የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶችና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

### 2.1.1. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት

ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ሲታሰብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ ለምሳሌ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገው ደረጃ ግቡን እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከሚጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ነው Little Wood (1981)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረፁት ዓበይት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት እንደመሆኑ መጠን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን Byrne (1981) ገልጸዋል፡፡

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል:: እውናዊውን የቋንቋ አጠቃቀም ስንመለከት ንግግር በማዳመጥ፤ ጽህፈት በንባብ የሚታገዝ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አላማም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቡ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው Gilbert (1982):: የቋንቋ ክሂሎችን አቀራረብ ስናስብ በአንድ መማሪያ ክፍል አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው፡፡ የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታለም የመጻፍ ክሂል አብሮ መምጣቱ አይቀርም፡፡ እንደዚህ

ዓይነቱን ትስስር የቋንቋ ባህሪይ የሚፈጥረው ቢሆንም በቋንቋ ትምህርት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ

Byrne (1981) እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው፡፡ የክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ከክፍለ ጊዜው የትምህርት ዕቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባውን ክሂል በዋናነት ትኩረት እንዲቸረው ለማድረግ ያስችላል፡፡ አክለውም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በእርስ ተሳስረው አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሂሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

እንዲሁም ( Rivers 1981) በበኩላቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚማሩበት ጊዜ ሌሎችንም ክሂሎች አብረው እንዲያዳብሩ ለምሳሌ ተማሪዎች በሳል ድርሰት እንዲጽፉ ከተፈለገ በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ መዳበር እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በጣም ጥሩ የሆነ አንብቦ የመረዳት ክህሎት የመናገርና የማዳመጥ ብቃት ካላቸው ጥሩ ጽሁፍ እንደሚጽፉ የታመነ ነው፡፡ በመሆኑም ጽህፈትን ስናስተምር ሌሎችም አብረው እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከምሁሩ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ ወይም እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

## 2.1.2.የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች

ክሂሎች የሚለያዩባቸዉ የየራሳቸዉ ባህሪይ ቢኖራቸዉም ተደጋጋፊ እንደሆኑ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከንባብ ክሂሎች ጋር በማጣመር የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን መጠቀም ተመራጭ ነዉ፡፡ የትምህርት ይዘቶች ለማስተማሪያነት ስነ-ዘዴ ማፍለቂያዎች እንደሆኑ Corder (1973) ይገልጻሉ፡፡ የቋንቋ ክሂሎች እንዴት ይዋኸዱ የሚለዉን ሀሳብ የተለያዩ ሞዴሎችን አስፍሯል፡፡ ከሞዴሎቹ ዉስጥ አንዱ ይዘት ተኮር ነዉ ፡፡ ይዘት ተኮር ይዘትን መሠረት ባደረገ መልኩ ክሂሎችን ማዋኸጃ ሞዴል ነዉ፡፡ ለምሳሌ፡ ቋንቋዉን ለአንድ ታላሚ ተግባር ማዋል፡፡ (ለምንድህስና፣ ለግብርና፣ ለህክምና ወ.ዘ.ተ… )

Celece-Muricia (1991) እና Oxford (2001) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ቀራጮች፣ መጽሀፍ አዘጋጆችና መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸው በተለይም ይዘትን መሰረት ያደረገ፣ ተግባር ተኮር የሆነ ወይም ሁለቱንም ዘዴዎች ያዋሀደ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ስለይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ እንመለከታለን፡፡ ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ በዋናነት ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም አማካኝነት ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት እየተማሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡

Celce-muricia (1991) ይዘት ተኮር ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን መሰረት በማድረግ እንዲረዱት የሚያደርግ አቀራረብ ነው ሲሉ Atkins etal (1996) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ክሂሎችን አዋሀደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግም በተጨማሪ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ይዘቶች በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማስቻልም ነው ይላሉ፡፡

ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ የቋንቋ ችሎታን ከማጎልበቱም በተጨማሪ ተማሪዎች የተለያዩ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲመረምሩና ቋንቋዉንም ለተለያዩ ይዘቶች መመስረቺያነት እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል፡፡ ይህ ዘዴ ቋንቋዉን በቀጥታ ሳይሆን በተለያዩ ይዘቶች አማካኝነት በአዉድና በትክክለኛ ሁኔታ አስደግፎ ስለሚያለማምድ ተማሪዎች ስለ ይዘቱ ለማወቅ እንዲጠይቁ፣ እንዲያነቡ እንድጽፉ ያደርጋል በማለት ገልጸዋል Corder (1973)፡፡

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ ዋና ዓላማ ቋንቋን ማስተማር በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር ባሻገር ሙሉዕ የቋንቋ ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ነዉ፡፡

### 2.1.3. የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ

Oxford (2001) የቋንቋ ክሂሎች ተናጠላዊ አቀራረብ በጥንታዊው የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ከመገደብ ባለፈ በሌሎችም ትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርግ እንደነበር በመግለጽ ለዚህም እንደ ምክንያት የገለጹት ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት የሚቀርጹ ባለሙያዎች የቋንቋ ትምህርቱን በቋንቋ ቅርጽ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የተነጣጠሉ የቋንቋ ክሂሎችን ማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የተማሩ ተማሪዎች ሊኖራቸው የሚችለው

የቋንቋ እውቀት ደግሞ ስለቋንቋው ከማወቅ ባለፈ በታላሚው ቋንቋ የመጠቀም ችሎታቸውን እንዳያጎለብቱና ተግባቦታዊ ብቃታቸው በተገቢው መጠን እንዳይጨምር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል በማለት ያብራራሉ፡፡ እንዲሁም McDonough and Shaw (1992) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አቀናጅቶ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ዋና ዋና ዋናዎቹ የተማሪውን ፍላጎት ማነሳሳት፣ የተማሪውን ግንዛቤ ማሳደግና የመማር ማስተማርን ሂደትን ማፋጠን መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን ነጣጥሎ ከማቅረብ ይልቅ አቀናጅቶ ማቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ይጠቀሳል፡፡ ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው ሲቀርቡ፤ ተማሪዎች በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል (Harpetal, Bill 1996)::

በመሆኑም ከዚህ በላይ ከቀረቡት ቅኝቶች በመነሳት አጥኚዉ ክሂሎች በቅንጅት ቢያቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ያምናል፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያ ስለክሂሎቹ ምንነትና አስፈላጊነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ስለ አንብቦ መረዳት ምንነት፣ የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፣ የጽህፈት ክሂል ምንነትና የጽህፈት ክሂል ትምህርት አላማ በተመለከተ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳትን በተመለከተ Grellet በመጥቀስ አለም (1991) እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት መሰብሰብ መቻል ማለት ነው፡፡ በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እያንገዋለለ በሙተው የሚፈልገውን አይነት ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ በዚህም አንዱን መሰረታዊ አሀድ ከመረዳቱም

ባሻገር የአሀዱን ዝርዝር በብቃት የሚገነዘብበት ሁኔታ የሚጠቃለለው እዚሁ ውስጥ ነው፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡

Smith (1985) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት አንባቢው ቀድሞ ይዟቸው ለተነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ማለት ነው፡፡ ጥያቄ መጠየቅ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ባህሪ ነው፡፡ አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ካገኘ በአንባቢውና በጸሀፊው መካከል ተግባቦት ይፈጠራል፡፡ ተግባቦት የሚኖረው ደግሞ መረዳት ሲኖር ነው፡፡ ሰለሞን (2003) የተለያዩ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ አንብቦ መረዳት የቃላትን ፍቺ መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍች ሊረዳ ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ ስላልሆነ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም፡፡ ነገር ግን የጽሁፉን ግልጽ መልእክት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን  መልእክት ለማጎልበትና ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሀሳቦች መረዳትን የሚመለከት ነዉ  ፡፡
በአንድ ጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልእክት መገንዘብ የአንብቦ መረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚህ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም፡፡ በግልጽ የተመለከተውን መልእክት መነሻ በማድረግ በመገንዘብና በመመርመር የሚደርስበትን ውስጣዊ መልእክት መረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም አንድ አንባቢ በጽሁፉ ዉስጥ የሚገኙትን አያያዦችን፣ ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡
እነዚህን መገንዘቡ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትለታል፡፡ ሆኖም የጽሁፉን ቅደም ተከተል የሀሳብ ፍሰት መገንዘብ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን  አረፍተ ነገሮች ተናጠላዊ መልእክት መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ አንዱ አረፍተ ነገር ከፊተኛው ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነት የተለይዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርሰስ በርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል፡፡

Shanehan (2006) አንብቦ መረዳት የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መረዳትንና በሚገባ መጨበጥን የሚገልጽ እሳቤ እንደሆነና የጸሀፊውን ሀሳብ ወይም መልእክት መለየትን፣ አውዳዊ ፍችዎችን መገንዘብንና ከአውዱ ውጭ የሆኑ ፍችዎችንም መረዳትን የሚያጠቃልል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በማስከተልም አንብቦ መረዳትን በሁለት ይከፍሉታል፡፡ አንደኛ በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት ነው፡፡ በዚህ ስርም በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች መገንዘብ፣ በግልጽ የተቀመጡ ድርጊቶች፣ ክስተቶችና ቅደም ተከተል ማስታወስ፣ በጽሁፍ ውስጥ

የሰፈሩ ተመሳሳይና ልዩነቶችን መለየትና የምክንያትና ውጤት ትስስር መግለጽን ያካትታሉ፡፡ ሁለተኛ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በምንባቡ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ይጠቁማል፡፡ ይህ አይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ መለየትንና ደጋፊ ሀሳቦችን ለይቶ ማወቅን ከምክንያትና ከውጤት ትስስር የተነሳ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ነገር መገመትን የሚመለከት ነው፡፡

Nuttal (1996) እንደገለጹት አንብቦ መረዳት ማለት ለንባብ የቀረበውን ጽሁፍና የአንባቢውን አእምሯዊ እውቀት እንዲሁም ስነ ልሳናዊ ችሎታ በሂደት በማገናኘት ለተጻፈው ጽሁፍ ትርጉም መስጠት ነው፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደተቻለው አንብቦ መረዳት ከጽሁፍ ውስጥ መረጃ መሰብሰብ መቻልን፣ የቃላትን፣ የጽሁፍን መልእክት፣ የአያያዦችን ሰዋስዋዊ አገባብ፣ የጽሁፍን ቅደም ተከተልና የሃሳብ ፍሰትን መገንዘብን፣ በተጨማሪም አንባቢው ቀድሞ ይዞት ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ መስጠትን በውስጡ የሚያካትት በአጠቃላይ በግልጽ የሰፈሩና ያልሰፈሩ ሀሳቦችን መረዳት መቻል ነው፡፡

## 2.2.1. የአንብቦ መረዳት ስልቶች

Harmer (1991) እንደገለፁት የተለያዩ ፅሁፎች ለተለያዩ አላማዎች ሲነበቡ አንባቢዎች የተለያዩ ስልቶችን መጠቀማቸው የግድ ነው፡፡ እነዚህም የንባብ ስልቶች የግርፍ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ፣ ሰፊ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ በማለት በአራት ተከፍለዋል፡፡ የግርፍ ንባብበ አጠቃላይ የተፃፈውን ጽሁፍ ሀሳብ ለማግኘት የሚነበብበት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት ከሚነበበው ጽሁፍ የየአንቀፁን መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ለመረዳት የምንጠቀምበት ነው፡፡ ሁለተኛው የንባብ ስልት ደግሞ የአሰሳ ንባብ የሚባለው ሲሆን፤ በፍጥነት የሚነበብበት ስልት ሆኖ ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ አንድ የተወሰነ መረጃን ነጥሎ ለማውጣት እና ለመረዳት የምንጠቀምበት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ቁጥርን ፣ ዓመተ ምህረትን እና ስምን ለመለየት ያገለግላል፡፡ ሶስተኛው ሰፊ ንባብ የሚባለው ደግሞ ብዙውን ጊዜ በቦታ እና በጊዜ ሳይወሰን አንባቢው ለመዝናናት ሲፈልግ የሚገለገልበት ስልት ነው፡፡ የሚነበበው ፅሁፍ ሰፊ በመሆኑ የፅሁፉንአጠቃላይ መልዕክት ለመገንዘብ የአንባቢውን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ የመጨረሻው ደግሞ ጥልቅ የንባብ ስልት የሚባለው ፅሁፉን በጥልቀት ለመገንዘብ ሲባል የፅሁፉ መጠን እንደ ሰፊ ንባብ ያልሰፋ በጊዜ እና በቦታ የተገደበ ሆኖ በንባብ ጊዜ ከፍጥነት ይልቅ በእርጋታ፣ በትኩረት እና በጥንቃቄ መከወንን

የሚጠይቅ ነው፡፡ በጥልቀት ንባብ ጊዜ በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ የሰፈሩ መረጃዎች ላይ ከማተኮር እንስቶ በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን እንድምታ እስከመስጠት የሚደረስበት የንባብ ስልት ነው፡፡ አንባቢው ከሚያገኘው ጠቀሜታ አንፃር ደግሞ ማንበብ ላዕላይ፣ ታህታይ እና አልቦ (ዜሮ) ንባብ በማለት በሶስት የንባብ ደረጃዎች የሚከፋፍሉዋቸው እንዳሉ ማረው (1998) Peyit (1998) ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡

ላዕላይ ንባብ አንባቢው ትኩረት በመስጠት የሚያነብበት ሆኖ አላማው የተሰጠውን ፅሁፍ በፍጥነት አንብቦ ለመጨረስ እና ሁሉንም ለመረዳት የሚሞከርበት ነው፡፡ ታህታይ የንባብ ደረጃ ደግሞ አንባቢው በሚያነበው ፅሁፍ ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ዋናውን መልዕክት መረዳት እና ከተገለፀው ሀሳብ በተጨማሪ ያሉ ጉዳዮችን መመልከት፣ የነገሮችን ዝምድና መፈተሽ ወዘተ ተግባራትን ለማከናወን የምንገለገልበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አልቦ (ዜሮ) የንባብ ደረጃ ያለምንም ትኩረት ፅሁፉን በፍጥነት አንብቦ መጨረስን የሚመለከት ነው (ማረው፣1998) ፡፡

የንባብ ትምህርት የተለያዩ ስልቶችን እንደሚጠቀም ተገልጿል፡፡ እነሱም የግርፍ፣ የአሰሳ፣ ሰፊ እና ጥልቅ ንባብ ናቸው፡፡ ከአንባቢው ጠቀሜታ አንፃር ደግሞ ላዕላይ፣ ታህታይ እና አልቦ (ዜሮ) ንባብ በማለት በሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህ ስልቶች የየራሳቸው የአነባበብ መንገድ አላቸው፡፡

### 2.2.2. የጥሩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄ ባህሪያት

በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ Madson (1983) ይገልጻሉ፡፡ Nuttal (1996) እና Madson (1983) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በማዛመድ፣ ትንበያ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በአጭር መልስ ስጥ፣ በፃፍ፣ በምርጫ፣ በክፍት ቦታ ሙላ መጠየቅ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

Hughes (1997) እንደገለጹት የአንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል፡፡

ሀ.ከሁሉም በፊት ጥያቄዎቹ በቀረበው ምንባብ ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት የግድ ምንባቡን ማንበብና መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በፈተናው ውስጥ ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሰረቱበትን ምንባብ ሳያነቡና ሳይረዱ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች መካተት የለባቸውም፡፡ ይሁን እንጅ አልፎ አልፎ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የሚዘጋጁ ፈተናዎች ይህ ባህሪ ይጎድላቸዋል፡፡ ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሰረቱበትን ምንባብ ሳያነቡ

ጥያቄዎቹን በትክክል ይመልሷቸዋል፡፡ የዚህም ምክንያቱ ጥያቄዎቹ በምንባቡ ላይ ባለ መመስረታቸውና ቅድመ እውቀትን ስለሚጠይቁ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ.በተቻለ መጠን የፈተናው ጥያቄዎች የተጻፉባቸው ቃላት ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች በቀጥታ ከምንባቡ የተወሰዱ ባይሆኑ ይመረጣል፡፡ ይህም ተፈታኞቹ ምንባቡን ሳይረዱ ቃላቱን ሀረጋቱን አረፍተ ነገሮቹን በማስታወስና ከምንባቡ በማገናዘብ ብቻ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ለመከላከል ያስችላል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆን ለፈተና የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የቀረበውን ንባብ መሰረት ያደረጉ ፈተናው የሚጠቀማቸው ቃላትና ሀረጋት ከንባቡ በቀጥታ የተወሰዱ ባይሆኑ ፈተናው የተማሪዎችን ችሎታ የሚለካ ይሆናል፡፡

## 2.3. የጽህፈት ክሂል ምንነት

ከቋንቋ ክሂሎች መካከል መጻፍ አንዱ ሲሆን የንግግር ድምጾችን በሚወክሉ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር የመግባባት ተግባር ነው፡፡ የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

Byrne (1991) ሲገልጹ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምጾች የየራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና ይሰጣቸዋል፤ ትዕምርቶቹ የቋንቋውን ሥርዓት ተከትለው ይዋሀዳሉ፡፡ እነዚህ ድምፆች ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ተቀናጅተው ይቀርባሉ ይህም ጽህፈት ይባላል በማለት አብራርተዋል፡፡ አክለውም ጽህፈት ድምፅን አቀናጅቶ ቃላት መመስረት ብቻ ሳይሆን እነዚያን ቃላትም በማቀናጀት ትርጉም ያለው ዓ.ነገርን ማዋቀርን፣ዓ.ነገሮችም አንቀጽንም መመሰረትን ወዘተ የሚያካትት ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ ብዙዎቹ የመስኩ ባለሙያዎች ይጋሩታል (Harmer 1991) እና (Nunan 1988)፡፡

Byrne (1991) ጽሁፍ በምንጽፍ ጊዜ ምልክቶችን እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ምልክቶች የሚፈጥሯቸው ፊደሎችና የፊደሎች ግንኙነት ሲሆን ከድምጹ ጋር ይገናኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር ከድምጽ በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም በግልጽ የሚታዩ ምልክቶችን ከማፍለቅ በላይ ነው ብለው በይነውታል፡፡ ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች እንደምንረዳው ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን በመጠቀም ሀሳብን፣ ስሜትን፣ መረጃን እንዲሁም መልዕክትን ማስተላለፊያና ቀርፆ ማስቀመጫ ክሂል ነው፡፡ በሚፃፍበት ወቅትም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምና ሥርዓት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ጽህፈት እንደ ቃላዊ ክሂሎች በመልመድ ሳይሆን በመማር የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ትጋትንና ጥረትን

የሚጠይቅ የቋንቋ መሠረታዊ ክሂል ነው፡፡ መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡

ስለዚህ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን የመጻፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለጻል፡፡ መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት Byrne (1991) ሲያስረዱ ሶስት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፡፡ እነሱም ስነ-ልቦናዊ ችግር፣ ሰዋሰዋዊ ችግርና ግንዛቤዊ ችግር ናቸው ፡፡ በመቀጠል ስለጽህፈት ትምህርት ዓላማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.3.1. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ

የጽህፈት ትምህርት ተቀዳሚ አላማ ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት ሀሳባቸውን በተቃና መንገድ በመግለጽ ጽሁፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ እንደ Raimes (1983) ገለጻ ተማሪዎች ጽህፈትን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ዓረፍተ ነገሮችን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ ይገባቸዋል በማለት ገለጻዎቹ የሚያካትቷቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡ እነሱም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት እና ከገጽ ለገጽ ተረክበውም ሃሳብን በጽሁፍ ለመግለጽ፣ ዕውቀትን ለማግኘት፣ ከእለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየትና በቋንቋው የሚጻፍ የጽሁፍ ሥራዎች በተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ማስቻል ናቸው፡፡ በተጨማሪም ምሁሩ ጽህፈትን መማር ሁለት ዓላማዎች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡ አንደኛው ጽህፈትን በዓብነት በማስተማር የጽሁፍ ተግባቦታዊ ክህሎች፣ ርተዕነት (Fluency) እና ትክክለኛነት (Accuracy) ማለማመድ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የታለመውን ቋንቋ ሥነ-ልሳናዊ ክህሎች ማለትም የቃላት፣ የሰዋሰው ወዘተ ችሎታ ማስተማር ነው፡፡ እንደ Brandy (1994) አገላለጽ የጽህፈትን ትምህርት ዓላማ ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታው አኳያም ሊታይ ይችላል፡፡ ጽህፈትን መማር ለግለሰቡ አመለካከቱን ለመግለጽና ለመደገፍ፣ አእምሯዊተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉ ሰነዶችን ለመመርመር ሲያግዘው ለማህበረሰቡም የጽሁፍ ቋንቋ ቅርጽ ለመያዝ፣ የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎችን ልዩልዩ መረጃ ለማጠናከር ያገለግላል፡፡

Heaton (1991) በበኩላቸው ጽህፈትን መማር የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን ተገቢነት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮችን የመጻፍ፣ ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ለአገልግሎት የማዋል፣ ተቀባይነት ያለውን ሃሳብ የመምረጥ፣ የማመንጨትና አስፋፍቶ የማቅረብ፣ ተፈላጊውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ አጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የዓረፍተ ነገር እና አንቀጽ አወቃቀር ሥርዓትን

ጠብቆ የመጻፍ፣ የተለመደ እና መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ወ.ዘ.ተ ለማዳበር ይረዳል ይላሉ፡፡ ጠቅለል ባለ አገላለጽ የጽህፈት ትምህርት ዓላማዎች የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋሰው ዕውቀትን በማጠናከር በጽሁፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን ማለማመድ ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር የመማሩ ዓላማ ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ማስገኘቱና ለጽሁፍ ተግባቦት አስፈላጊ የሆኑትን ክሂሎች ለማዳበር ማገዙ ተጠቃሽ ነጥቦች ሲሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጪ የሚሰሩ የጽህፈት ትምህርት ተግባራዊ ድርሻቸው ጉልህ ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከታለመው ቋንቋ የሚጠበቁትን ክህሎች እና ዕውቀቶች ማስጨበጥ ነው፡፡

የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችም የራሳቸው የሆኑ ዓላማዎች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ አንደኛው ኣላማ የተማሪዎችን ቋንቋ እውቀት ማለትም የቃላትና የሰዋሰው ችሎታ ማጠንከር ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ተማሪዎችን ተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡

በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት መልመጃዎች ዓላማ የተማሪዎችን የቃላትና ሰዋሰው እውቀትን በማጠናከር በጽሑፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል ነው፡፡ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግር መግለጽ እንደሚችሉ ሁሉ በአእምሮአቸው የሚመሳሰሉትን ሀሳቦች በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው መዳበር አለበት፡፡ ይህም ከሚያዳምጡት እና ከሚያነቡት ተነስተው የሚረዷቸውን ሀሳቦች መዝግቦ ለመያዝ ይጠቅማቸዋል፡፡ በሂደቱም የቋንቋውን ምልክቶች ከመለየት ባሻገር ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን እንዲያውቁ ያግዛቸዋል፡፡

## 2.4. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር

በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ያላቸው በመሆኑ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ መጻፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል፤ ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱን፣ የታሪክ አወቃቀሩንና የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸው ለሚጽፉት ጽሁፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ይህም ሂደት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር የሚያመለክት መሆኑን Harpetal (1996) ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡
የሁለቱ በውህደት መቅረብ የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ክሂሎቹ የቀደመ እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸውም እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ May (1990) በተመሳሳይ ተማሪዎቹ ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል፡፡ ይህም የሚያሳየው በክሂሎቹ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ያመለክታል፡፡ አንባቢዎችና ፀሀፊዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመስታዎት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን የቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው፡፡ አንባቢዎችና ፀሀፊዎች ለማንበብና ለመጻፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ ይኸውም ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፤ ፍላጎትም ይኖራቸዋል፤ የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤ አእምሯዊ ምስል ይፈጥራሉ፡፡

የፀሀፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የሁለቱ የመግባቢያ መንገዳቸው የተዘጋጀው በጽሁፍ ነው፡፡ የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ ሃሳብ ለመጋራት ወይም ለመዝናናት ጽሁፍ ማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ባለጉዳዮች ማለትም ፀሀፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሁፍ ይገናኛሉ በማለት አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

## 2.4.1. የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍን ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ ጠቀሜታ

አንብቦ መረዳት የተለያዩ ክሂሎች የተዋሀዱበት ሂደት እንደሆነ Ellis and Brain (1980) ይገልጻሉ፡፡

እንደ Grellet (1991) ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መንገዶችን በማመቻቸት የተለያዩ አይነት ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡ ጥያቄዎችም ከምንባቡ አጠቃላይ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ

ዝርዝርና ግልጽ የተቀመጡ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጥያቄዎቹ አይነትና ተግባርም የተወሰነ ክሂል ከማዳበር ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ለተማሪዎች በሚወጡ ጥያቄዎች አማካኝነት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ጥያቄዎቹ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችንም ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማንባብና መጻፍ በንባብ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች አብረው ሊያዳብሩት ከሚጠበቅባቸው ክሂሎች ውስጥ አንዱ መጻፍ ነው፡፡

የመጻፍ ክሂል በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት እንዲዳብር ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራትን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣ ሀሳባቸውን ባጭር ባጭሩ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው በተወሰነ መልኩ እንዲያቀርቡ እና አጫጭር ሃሳቦችን አብራርተው በዝርዝር እንዲጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች የመጻፍ ክሂልን ከንባብ ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲዳብር የሚያግዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንብቦ መረዳት ከሌሎች ክሂሎች ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት ሌሎች ክሂሎች ተዋህደው እንዲዳብሩ ማድረግ እንደሚቻል እንረዳለን፡፡

Conley (1997) የማንበብና የመጻፍ ክንዋኔዎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ማንበብና መጻፍ በእለት ተእለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉምን መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝበዋል፡፡ በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ በመሆናቸው ነው፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ክሂሎቹን በቅንጅት ለማዳበር የሚጠቅሙ ብልሃቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 2.4.2. የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች

አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ ለአብነት ያህል ጥቂቶችን ለማየት እንሞክራለን፡፡

Block (1997) ሲገልጹ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሁፍ ማቀናበርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለል፣ መተንበይና መገመት በጥልቀት ማሰብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

***ሀ. ጥያቄ መጠየቅ***፡- በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡

Block (1997) ሲገልጹ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣምረው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው ሲሉ፤ Airasian (1997) በበኩላቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣ በጥልቀት እንዲያነቡና ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Gary (1995) ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድነው? ያወቅኩት ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያሳድግላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡

***ለ.መተንበይና መገመት*** **(Inferring and predicting)፡-** ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለ ቀጥሎ የሚመጣውን ሁነት ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቁምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው፡፡ መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኝን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቁምበት ልዩ ስልት ነው::

እንዲሁም Barrs (2000) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንድን ጽሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገጸባህሪያትን ማንነት፣ ድርጊት፣ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይህም

የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ጽሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመጻፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ብልሃቶች አማካኝነት ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ ጥረት የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎቹ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ ትርጉም ይሰጣሉ፣ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ስላነበቡት ወይም ስለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ብልሃት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

**ሐ.ማጠቃለል** (Summarizing)፡- ማጠቃለልን በሚመለከት Block and Mangeri (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሁፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በዕለት ተዕለት ህይወት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችላቸውን ብልሃቶች መማር ይኖርባቸዋል፡፡

**መ. ምሰላ** (Imaging):- አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ገጸ ባህሪያት፣ድርጊትና ሁነቶች በአእምሮ ምስል የሚቀረጽበት ስልት ምሰላ ይባላል፡፡ ይህንንም ለአንባቢዎችና ለጸሀፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ በንቃት እንዲያነቡ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ ይህም ብልሃት በህይወት ውስጥ ስሜታዊ ገጠመኞችን ከአመለካከትና ከተጠየቃዊ ገጠመኞች ጋር ለማቀናጀትም ይጠቅማል፡፡ በቋንቋው ሂደት ውስጥ በራሱ ሳይሆን

የቋንቋው ሂደት በሚፈጥረው ገጠመኝ ውስጥ ጠልቆ ለመግባት ያስችላል፡፡ ምስል ከሳች ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ እያነበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲናገሩ በማድረግ እያነበቡ እያሉም ምስላቸው እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ በመጠየቅም ማለማመድ እንደሚቻል Block (1997) አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እያደራጁ እንድጽፉ የሚያደርግ ልሆን ይገባል፡፡ ክንዋኔውም ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ መያዝ ሊሆን ይችላል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል፡፡ በመጨረሻም መምህራኑ የተማሪዎችን ስራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶች የሚያስፈልጋቸው ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጥያቄዎችም ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቀራኙ የመጻፍ ተግባሮች በጽሁፍ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gary 1995)::

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳናቱ የቀረቡት ጥናታዊ ግኝቶች አንብቦ የመረዳትና የመጻፍን ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች የማይነጣጠሉ፣ የሚደጋገፉና ትስስር ያላቸው መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ክሂሎቹን በቅንጅት ተከታታይ በሆነ መልኩ ማቅረብ ከተቻለ የተማሪዎችን በራስ የመተማመንን ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው፣ የተማሪዎችን ግንዛቤ እንደሚያሳድግላቸውና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውም ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት አጥኚዉ የመስኩ ተመራማሪዎች ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማር ያቀረቧቸውን ብልሃቶች ተግባር ላይ በማዋል ዉጤታማነቱን ለመፈተሽ ይህንን ጥናት ለማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደምት ስራዎችን ቅኝት እንመለከታለን፡፡

## 2.5. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የጥናቱ አቅራቢ በመረጠዉ ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሩ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዷል፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ትኩረት የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ በመሆኑ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶችና ወይም ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን ተቀራራቢነት ካላቸው ቀደምት ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

**አታኽልቲ መኮነን** (1998) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም የቋንቋ መምህራን ክሂሎችን እንዴት አቀናጅተዉ እንዳቀረቧቸው የሚቃኝ እና ክሂሎችን እንዴት አቀናጅተው እንደማያቀርቧቸው የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የአታኽልቲ ጥናት የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከቋንቋ ክሂሎች ዉስጥ የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ ስለሆነ ከዚህ ጥናት ጋር በትኩረት ይለያል፡፡

**እመቤት እሸቴ** (2011) አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና (በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት) በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችዉ ነበር፡፡

የጥናቷ ዋና ትኩረት የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ የይዘት አቀራረብ ትናተና ላይ ነዉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ በመሆኑ ይለያል፡፡

**ሞገስ አመራ** (1999) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና" ለማረጋገጥ ጥናት አድርገዋል፡፡

በጥናቱ ውጤትም በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በውህደት የሚቀርቡበት ሁኔታ ትኩረት ያላገኘ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናት በአንጻሩ ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

የሞገስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ከሞገስ ጥናት የሚለየው የሞገስ ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ማረጋገጥ ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ ስለሆነ እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣ በጊዜና በቦታ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

**እሸቴ መብራት** (2003) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነዉ፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ በወረታ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡

የጥናቱ ውጤትም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ካላቸው ትስስርና ዝምድና አንጻር በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ በውህደት ቢቀርቡ ለክሂሎቹ መጎልበት የላቀ ሚና እንዳለው አሳይቷል፡፡ የእሸቴ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ላይ እና በሙከራዊ ጥናት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ከእሸቴ ጥናት የሚለየው የእሼቴ ጥናት በአስረኛ ክፍል የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ማረጋገጥ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ ላይ ያተኮረ ነዉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና አካሄድ

በምዕራፍ ሶስት ስር የጥናቱ ንድፍ እንዴት እንደተዘጋጀ፣ የጥናቱ አካሄድ፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት፣ የተጠኚ ተማሪዎች የስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች እና የመረጃ አተናተን ዘዴን በዝርዝር ቀርቦበታል፡፡

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

በርካታ የምርምር አይነቶች ቢኖሩም ይህ ጥናት የተከተለው ከፊል ሙከራዊ የምርምር ስልትን ነው፡፡ ከመረጃ መተንተኛ አንጻር መጠናዊ ምርምርን ተከትሏል፡፡ መጠናዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ያለዉ (2009) መጠናዊ ምርምር መጠንን ገላጭ፣ የመረጃዎቹ አይነት በቁጥር የሚገለፁ፣ መረጃዎቹ የሚተነተኑት በስታቲስቲካዊ ዘዴ እንደሆነና በአብዛኛዉ መላምትን ተመርኩዞ የሚካሄድ የምርምር አይነት ነዉ በማለት አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመራማሪዉ በመረጠዉ ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ ያነሳቸዉን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት የሚያደርግ የምርምር አይነት ነው በማለት ገልፀውታል፡፡

ከላይ ከቀረበዉ ሀሳብ በመነሳት መጠናዊ ምርምር መረጃዎችን በስታቲስቲካዊ ዘዴ የሚያቀርብና መላምትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ለዚህ ጥናት አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ለጥናቱ ተመርጧል፡፡ የዚህ ጥናት ዉጤትም መጠናዊ በሆነ መንገድ በቲ-ቴስት በማነፃፀር በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታቲስቲክስ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ይህ ጥናትም ሁለት ተጠኚ ቡድኖችን የያዘና የሁለቱ ቡድኖች ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ተግባራዊ ያደረገ ነው፡፡

## 3.2. የጥናቱ አካሄድ

ይህ ጥናት የሚካሄድበት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ሥር ከሚገኙ 21 ወረዳዎች መካከል በሠኮሩ ወረዳ ነዉ፡፡ የሰኮሩ ወረዳ ስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለዉ ሲሆን ይህ ጥናት የሚካሄድበት በሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነዉ፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ሲሆን፤ ጥናቱ ያተኮረው በኦሮሚያ ክልል በጅማ

ዞን ሰኮሩ ወረዳ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ አመራረጣቸዉም እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡

## 3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሰኮሩ ወረዳ ከሚገኙ ስድስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሰኮሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይኸውም አጥኚዉ በዚህ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እያገለገለ ስለሆነ ጥናቱን ለማካሄድም ሆነ መረጃ ለመሰብሰብ ጥናቱን ቀናና ቀልጣፋ ያደርግልኛል ብሎ በማሰቡ ነው፡፡

## 3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በጥናት ተተኳሪዉ ትምህርት ቤት የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በትምህርት ቤቱ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ የክፍል ደረጃን የያዘ ሲሆን፣ ለጥናቱ የተመረጠዉ የክፍል ደረጃ በአስረኛ የክፍል ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በcovid-19 ምክንያት ትምህርታቸዉን ዘግይተዉ በመጀመራቸዉ ምክንያት ያልተመረጡ ሲሆን አስራ አንደኛ እና አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በcovid-19 ምክንያት ትምህርታቸዉ በሳምንት ለሶስት ቀናት ብቻ ስለሚማሩ የትምህርት ጫና ስለሚኖርባቸው በማሰብ እና  አጥኚዉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ያለ ስለሆነ ለጥናቱ ምቹ ይሆንልኛል ብሎ በማሰብ የክፍል ደረጃዉን መርጧል፡፡

## 3.3.3. የተማሪዎች አመራረጥ

በሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ የክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የቁጥር ብዛት ወንድ 237 ሴት 300 በድምሩ 537 ነው:: የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ዘጠኝ ሲሆን፣ በአንድ የመማሪያ ክፍል  በአማካይ 60 ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ተማሪዎቹ በሁለት ፈረቃ  የሚማሩ ሲሆን ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ለማሳተፍ አስቸጋሪ ነዉ፡፡ በመሆኑም ከዘጠኝ የመማሪያ ክፍሎች የሁለት ክፍል ተማሪዎችን በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ  በመጠቀም በሁለት የመማሪያ ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በዕጣዉም መሰረት የተመረጡት ተማሪዎች በ10B፣ እና በ10ኛI ክፍል ዉስጥ የሚማሩ 120 ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ተማሪዎቹን ለቁጥጥርና ለሙከራ ቡድን ለመክፈል የችሎታ ደረጃቸዉ ተመጣጣኝ መሆኑን ለማወቅ የቅድመ ትምህርት ፈተና ተስጥቷቸዋል፡፡ በፈተናዉም መሠረት ተቀራራቢ ዉጤት ያመጡትን 50 ተማሪዎች በመዉሰድ

በተራ የዕጣ ናሙና ስልት በሁለት ቡድን በማካፈል እያንዳንዳቸው 25 ተማሪዎች ባላቸው ሁለት ምድቦች በመክፈል 25 ተማሪዎችን ለሙከራ ቡድን የቀሩትን 25 ተማሪዎችን ደግሞ ለቁጥጥር ቡድን ዉለዉ በሁለት የተለያየ ፈረቃ የማስተማሩ ስራ ተከናውኗል::

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኝ የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸዉ፡፡

### 3.4.1. ፈተና

በዚህ ጥናት ፈተና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነዉ፡፡ ዓላማውም የጥናቱን ተሳታፊዎች የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ለመፈተሽ፤ ለተጠኚ ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርት ፈተና በአጥኚዉ ተዘጋጅቷል፡፡ በቅድመ ትምህርት ፈተና የቀረበዉ የፈተናዉ ይዘት፣ አዘገጃጀቱና የፈተናዉ አስተራረምን በተመለከተ፤ ፈተናዉ ሁለት ምንባቦችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያዉ ምንባብ በገላጭ የድርሰት አጻጻፍ የተጻፈ ምንባብ ነዉ፡፡ ከመጀመሪያዉ ምንባብ የተዘጋጀው ፈተና ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ የሚመለሱና የምንባቡን ታሪክ በአንድ አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ የሚያዝ ጥያቄ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ የቀረበላቸዉን ምንባብ በማንበብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀጽ የሚጻፍ ትዕዛዝ ይዟል።

(አባሪ“6 ”ይመልከቱ)፡፡

የፈተናውን አስተማማኝነትና ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ ሲባል በአጥኚዉ አማካሪና ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሞ ለፈተናው የቀረበው ጽሁፍ ረጅም በመሆኑ እንዲያጥርና ጥያቄዎቹ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን የሚመለከት ስለሆነ የጥያቄዎቹ ብዛት ከአስራ አምስት ወደ አስር ዝቅ እንዲል የማሻሻያና አስተያየት ተሰጥቶበት ተሻሽሎ ከተዘጋጀ በኋላ የቅድመ ፈተናዉን አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ ሲባል ተጠኚ ተማሪዎች ከመፈተናቸው በፊት በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ በሚመሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተናው ተሰጥቶ በክሮንባች አልፋ (Cronbach Alpha) ዘዴ ተሰልቶ 0.609 በመሆኑ አስተማማኝነቱ ስለተረጋገጠ የቅድመ ትምህርት ፈተና ለጥናቱ ለመረጡት120 ተማሪዎች ፈተናዉ ተሰጥቷል፡፡ ፈተናው የታረመው ከ60% ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል45 ነጥብ የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል15 ነጥብ ይዟል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ጥናቱ ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን የተማሪዎቹን የችሎታ ደረጃ ለማወቅ ቅድመ ትምህርት ፈተና ለ120 ተማሪዎች ተሰጥቷል፡፡ ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ 1፡00 ስዓት ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተናው የመልስ ወረቀት በአጥኚዉ ተሰብስቧል፡፡ ከዚያም በተዘጋጁት የማረሚያ መልሶች መሰረት ፈተናው በሶስት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሟል፡፡ (አባሪ "1 "ይመልከቱ)፡፡

የውጤት አሰጣጡ በሶስት የተለያዩ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ተደምሮና ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ ዋና ውጤት ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት መሰረት ተቀራራቢ ውጤት ያላቸውን 50 ተማሪዎችን በመዉሰድ ተራ የናሙና ዘዴ በመጠቀም 25 ተማሪዎችን ለሙከራ እና 25 ተማሪዎችን ለቁጥጥር ቡድን ዉለዋል፡፡( አባሪ "2 "ይመልከቱ)፡፡

ከዚህም በመቀጠል የጥናቱ ተሳታፊዎች የሙከራ ቡድኑ  አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ይረዳሉ የተባሉትን ብልሃቶች ለመጠቀም በመማሪያ መጻፋቸዉ ዉስጥ የተካተቱትን ምንባቦችን በመዉሰድ ቅድመ ንባብ፣ ጊዜ ንባብ፣ ድህረ-ንባብ ጥያቄ በመጠየቅ፣ ቀጥሎ የሚመጣዉን ሀሳብ እንድተነብዩ በማድረግ፣ ስላነበቡት ጽሁፍ  ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሁፍ በአእምሯቸዉ የታሰባቸዉን በጽሁፍ እንዲያጠቃልሉ በማድረግና በጽሁፉ ዉስጥ ያሉትን ገጸ-ባህሪያት፣ ድርጊትና ሁነቶችን በእእምሯቸዉ ዉስጥ ምስል እንዲቀርጹ በማድረግ የታያቸዉን ምስል በጽሁፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ በተጨማሪም **ማስታወሻ እንዲይዙ በማድረግ፣  ሀሳባቸውን ባጭር ባጭሩ በጽሁፍ  እንዲያቀርቡ እና አጫጭር ሃሳቦችን አብራርተው በዝርዝር እንዲጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች** በተዘጋጀው የማስተማሪያ ፅሁፍ ለአራት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን በየቀኑ ለአንድ ስዓት፤ የቁጥጥር ቡድኑ ወትሮ በሚማሩት ስልት ከተማሩ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር በተመሳሰለ መልኩ ተዘጋጅቶ በአጥኚዉ፣ አማካሪና ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግሞ  ልክ እንደ ቅድመ ፈተናዉ ድህረ ፈተናው በቅርብ ርቀት ለይ በሚገኝ ደነባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑ ተደርጎ በክሮንባች አልፋ (Cronbach Alpha) ዘዴ ተሰልቶ 0.701  በመምጠቱ ፈተናው አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ  ፈተናዉ ተሰጥቷቸዋል፡፡ (አባሪ "7 " ይመልከቱ)፡፡

እርማቱም የቅድመ ትምህርት ፈተናውን ባረሙት የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከናውኗል፡፡

### 3.5. የማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን የአንብቦ መረዳት ክሂልንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር በክፍል ደረጃው የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ Oxford (2003) እንደሚያስረዱት በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያው ተገቢነት፣ ክብደትና ቅለት ነው፤ ለዚህም በሙከራዊ ጥናት በተማሪዎች ውጤት ያመጣውን ለውጥ ለማረጋገጥ ለዚያው የክፍል ደረጃና በዚያው ስርአተ ትምህርት ውስጥ ያሉ ምንባቦችንና መልመጃዎች መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም መማሪያ መጽሐፉ የተማሪዎችን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክፍል ደረጃው ተመጥኖ የተዘጋጀ በመሆኑ ይህን ተላውጦ ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናትም አዲስ የማስተማሪያ መሳሪያ በማዘጋጀት ምክንያት የሚፈጠረውን ተላውጦ ለመቆጣጠር በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ምንባቦችንና ተግባራትን ለመጠቀም ተችሏል፡፡ መማሪያ መጽሐፉን መሰረት አድርጎ የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል በቅንጅት ማስተማር ለሙከራዉ፤ ያለቅንጅት ወትሮዉኑ በሚማሩት መንገድ የተከተሉ ናቸው፡፡

Block (1997) የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Oxford (2003) የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎቹን አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር የሚቻለዉ ብልሃቶቹን በአውድ ሊያለማምዱ የሚችሉ ምንባቦች የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል ማለማመጃ መልመጃዎች ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለሙከራ ቡድኑ የቀረቡት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል በቅንጅት የማስተማር ብልሃት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች በመጠቀም ተማሪዎቹ እንዲማሩ ተደርጓል ማስተማሪያ ዘዴ (አባሪ “ 8 ” ይመልከቱ)፡፡

በትምህርቱ ጊዜም ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበውን ሁለት ክፍለ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትንና የታቀዱትን ተግባራት ለመሸፈን የሚያስችል አልነበረም፡፡ ስለዚህ ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት በተቃራኒ ፈረቃ በማመቻቸት ከትምህርት ሰዓት ውጭ ፕሮግራም በማስያዝ ሁለቱም ቡድን

በተቃራኒ ክፍለ ጊዜ በሳምንት ሁለት ጊዜ (አንድ ክፍለ ጊዜ 1፡00 ሠዓት ያህል ለሙከራ ቡድኑ በተዘጋጀው ማስተማሪያ መሰረት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል በቅንጅት የማስተማር ብልሃቶቹን በመጠቀም እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የቁጥጥር ቡድኑ ግን በመጽሐፉ የቀረቡትን ትምህርት ይዘት ምንም አይነት ብልሃት ሳይታከልበት በመማሪያ መጽሐፉ ትምህርት አቀራረብ (በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ) መሰረት ተምረዋል፡፡

## 3.6. ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች

ጥናቱን ለማካሄድ በመጀመሪያ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የትብብር ደብዳቤ ተጽፏል፡፡ ከዚያም የትብብር ደብዳቤውን በመያዝ፣ ጥናቱ በሚካሄድበት ጅማ ዞን ሰኮሩ ወረዳ የሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ጋር ስለጥናቱ አላማ፣ ባህሪና ሂደት በመግለጽና በመወያየት ጥናቱ እንዲካሄድ ፈቃድ ተጠይቋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለጥናቱ በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ ከተመረጡት ሁለት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በመገናኘት የጥናቱን አላማ በማስረዳት ፈቃደኛ መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ሙሉ ፈቃደኛ በመሆናቸዉ ለሙከራ ቡድንና ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን ለመመደብ ከሁለቱ የ10ኛ ክፍል 120 ተማሪዎች የቅድመ ትማህርት ፈተና ወስደዋል፡፡ በቅድመ ትምህርት ፈተናዉ ተቀራራቢ ዉጤት ያገኙ 50 ተማሪዎችን በመዉሰድ በተራ የናሙና ዘዴ 25 ተማሪዎችን ለሙከራ ቡድን 25 ተማሪዎችን ደግሞ ለቁጥጥር ቡድን ተመድበዉ ሁለቱ ቡድኖች በተቃራኒ ፈረቃ ትምህርቱን ተከታትለዋል ፡፡

## 3.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱ መረጃ መተንተኛ ዘዴ መጠናዊ (Quntitative data analaysis method) ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተና የተሰበሰበ ሲሆን በቅድመ ትምህርት ፈተና ተጠኚ ተማሪዎቹ የችሎታ ልዩነታቸዉን ለማወቅ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ከዚያም የጥናቱ ተሳታፊ ቡድኖች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት ያላቸውን የችሎታ ደረጃ ለማወቅ የተፈተኑት ቅድመ-ትምህርት ፈተና ለየቡድኖቹ በገላጭ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖር ለማወቅ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትኗል፡፡ ትምህርቱ እንደተጠናቀቀ ሁለቱ ቡድኖች የተፈተኑትን ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤትም ለየቡድኖቹ በገላጭ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡

በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶቻቸው መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥም በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትነዋል፡፡

ቅድመ-ትምህርትና ድህረትምህርት የቡድኖች ንጽጽር ባለው ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ስልት የሚመሰረቱ ቡድኖች ፍጹም ከምርጫ መዛባት (selection bias) ነጻ ሊሆኑ ስለማይችሉ የሚገኘው ውጤት በጥንቃቄ መተርጎም አለበት፡፡ ይኸውም የሁለቱን ቡድኖች ድህረ-ትምህርት ውጤቶች ልዩነት በማየት ውጤቱን መተርጎም በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የልዩነቱ መነሻ ከተሳታፊዎች የባህርይ ልዩነት ይሁን ካለፉበት የልምምድ ሁኔታ ልዩነት የተገኘ መሆኑን መወሰን ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም የእያንዳንዱን ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ውጤቶች ልዩነት በማወዳደር የውጤት ትርጓሜውን መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ ለዚህም በእያንዳንዱ ቡድን በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን በማነጻጸር በጳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የጥናቱ ወጤት ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የጥናቱ ዉጤት ትንተና

የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰበዉ በፈተና ሲሆን የመረጃ አሰባሰቡ በቅድመ ትምህርት እና ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና የተሰበሰበ ነዉ፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለትንተና እንዲያመቹ ሆነው ተጠናቅረዉ የፈተናዎቹ አማካይ ውጤቶች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ( independent samples t- test)፣ በጻግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (paired samples t-test) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው የትንተናው ክፍል ያተኮረው ቅድመ ትምህርት ወይም ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ከመመማራቸዉ በፊት የችሎታ ልዩነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት መረጃው በገላጭ እና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፤ ውጤቱም በሠንጠረዥ 1 እና 2 እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ1. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታተስቲክስ**

| ቡድን | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት( mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት(std.Error mean) |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 27.4666 | 2.672 | 0.534 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 27.4266 | 2.993 | 0.598 |

ሠንጠረዥ1.የቁጥጥሩንና የሙከራውን ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (27.466) ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት (27.426) በ 0.04 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.993) ከሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት

ፈተና መደበኛ ልይይት (2.672) በ 0.324 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ተቀራራቢ ነው፡፡

በትንተናው መሰረት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት በ0.04 እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ2 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 2. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት**

| ቡድን | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት( mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | የነጻነት ደረጃ (d/f) | የቲ- ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ (sig 2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 27.4666 | 2.672 | 0.534 | 0.05 | 0.960 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 27.4266 | 2.993 | 0.598 | | |

ሠንጠረዥ 2. በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ (t= 0.5, p= 0.960) አሳይቷል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች ክሂሎቹን ከመማራቸው በፊት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል የችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

የጥናቱ መላምት ጥያቄዎች “የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በተጠኚ ቡድኖች መካከል የችሎታ ልዩነት ይኖራል፡፡” “የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በተጠኚ ቡድኖች መካከል ምንም የችሎታ ልዩነት አያመጣም::” በሚሉ መላምቶች ተማሪዎቹን በሙከራና ቡድንና በቁጥጥር ቡድን በመመደብ የተጠኑ መላምቶችን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 3 እና 4 ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ3. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ**

| ቡድን | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት( mean) | መደመኛ ልይይት(Std.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት(std.Error mean) |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 40.306 | 2.264 | 0.453 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 32.293 | 2.992 | 0.598 |

ሠንጠረዥ 3. የቁጥጥሩንና የሙከራውን ቡድኖች የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (40.306) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት (32.293) በ8.013 በልጦ ታይቷል፡፡

ትንተናው የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት በ8.013 ብልጫ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው

ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 4 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሠንጠረዥ 4. የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

| ቡድን | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት(mean) | መደመኛ ልይይት(Std.) | የነጻነት ደረጃ (d/f) | የ ቲ- ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ(sig 2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 25 | 40.306 | 2.264 | 48 | 10.676 | .000 |
| የቁጥጥር ቡድን | 25 | 32.293 | 2.992 | | | |

**ሠንጠረዥ4.** በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t=10.676, df =48, p= .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር በሚረዱ ብልሃቶች የተማሩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ደረጃ ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን አሳይቷል፡፡ ከዚህም የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር በሚረዱ ብልሃቶች ማስተማር ከተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ በበለጠ ሁኔታ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም “የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ያሻሽላል በሚል መላምት በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የችሎታ ልዩነት ያመጣል?” የሚለው

የጥናቱ አማራጭ መላምት አወንታዊ መልስ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም "አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር  በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ልዩነት አያመጣም" የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ በመሆን "የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ያሻሽላል" ፡፡ የሚለው ተለዋጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ከድህረ-ትምህርቱ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ የችሎታ ፈተና በተገኘው ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር በሚረዱ ብልሃቶች በመማር የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል ችሎታቸዉ  ለውጥ አሳይቷል፡፡

በክፍል ውስጥ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር በሚረዱ ብልሃቶች በመማር የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤታቸው ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዲኖረው አዎንታዊ ፋይዳ እንዳለው በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህም የተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ መሻሻል በርግጥም በብልሃቶቹ በመማራቸዉ ምክንያት መሆኑን አመላክቷል፡፡

ይህንንም ይበልጥ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ቡድን በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት ያስመዘገበውን የፈተና ውጤት በማነጻጸር መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የሙከራ ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት የፈተና ውጤቶች መካከል ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.5 እና 4.6 ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 5. የሙከራዉ ቡድን የቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ**

| ፈተና | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት(Std.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (std.Error mean) |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 27.466667 | 2.6718695 | .5343739 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 40.306667 | 2.2647049 | .4529410 |

በሠንጠረዥ5. የሙከራውን ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት (40.306) ከቅድመ-ትምህርቱ የፈተና አማካይ ውጤት (27.466) በ12.466 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.264) ከቅድመ-ትምህርቱ ፈተና መደበኛ ልይይት (2.671) በ-0.407 አንሶ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት የፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት ያለው ነዉ፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርቱ የፈተና አማካይ ውጤት በ12.466 እንደበለጠ ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 6 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሠንጠረዥ6. የሙከራዉ ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

| ፈተና | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | የነጻነት ደረጃ (d/f) | የቲ-ዋጋ(t-value) | የጉልህነት ደረጃ(sign. 2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 27.466667 | 2.6718695 | 48 | -18.33 | .000 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 40.306667 | 2.2647049 | | | |

ሠንጠረዥ 6 የሙከራው ቡድን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ የፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ ( t = -18.33, df = 48, p = .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በብልሃቶቹ ከተማሩ በኋላ በፊት ከነበራቸው ችሎታ የበለጠ መሻሻል ማሳየታቸውን ማየት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የማስተማሪያ ዘዴው የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ረድቷቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ውጤት ማስመዝገቡን የሚያሳየውን በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት የተገኘውን ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በተመሳሳይ በቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት የፈተና ውጤቶች መካከል ልዩነት ስለመኖሩ የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር በማድረግ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 7 እና 8 ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 7. የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ**

| ፈተና | የናሙና ብዛት(n) | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት(Std.) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (std.Error mean) |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 27.426667 | 2.9930777 | .5986155 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 32.293334 | 2.9927684 | .5985537 |

**ሠንጠረዥ7.** የቁጥጥር ቡድኑን የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት (32.293) ከቅድመ-ትምህርቱ የፈተና አማካይ ውጤት (27.426) በ4.867 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የድህረ- ትምህርቱ ፈተና መደበኛ ልይይት (2.992) ከቅድመ-ትምህርቱ ፈተና መደበኛ ልይይት (2.993) በ-0.001 አነሶ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከትምህርቱ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የፈተና ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት እንደ ሙከራዉ ቡድን የጎላ ባይሆንም ከቅድመ-ትምህርት የፈተና ዉጤት የተሻለ ዉጤት ማስመዝገባቸዉን ማየት ይቻላል፡፡

ትንተናው የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርቱ የፈተና አማካይ ውጤት በ4.867 እንደበለጠ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 8 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሠንጠረዥ 8. የቁጥጥር ቡድን ቅድመ-ትምህርትና ድህረ -ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ- ቴስት**

| ፈተና | የናሙና ብዛት (n) | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | የነጻነት ደረጃ (d/f) | የቲ-ዋጋ( t-value) | የጉልህነት ደረጃ(sig 2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ-ትምህርት | 25 | 27.426667 | 2.9930777 | 48 | -5.749 | .000 |
| ድህረ-ትምህርት | 25 | 32.293334 | 2.9927684 | | | |

**ሠንጠረዥ** 8 በቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= -5.749, df = 48, p= .000) አሳይቷል፡፡ ከዚህም የቁጥጥር ቡድኑ

ተማሪዎች በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ እንደ ሙከራ ቡድኑ የጎላ ባይሆንም የተወሰነ ለውጥ እንዳመጡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ቀደም ሲል በነጻ ናሙናዎች ቲ- ቴስት የተገኘው ውጤት የሙከራው ቡድን ድህረ-ትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ እንደበለጠ የሚያሳየውን ያረጋግጣል፡፡ በመጨረሻም አጠቃላይ የጥናቱን የመላምት ጥያቄዎችን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በሠንጠረዥ 9 እንደቀረበዉ ነዉ፡፡

**ሠንጠረዠ 9. የመላምት ፍተሻ ዉጤት** (two tailed) የt-ቴስት ስሌት

| ፈተና | የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | | የተሰላ የቲ-ዋጋ | የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ | የጉልህነት ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ናሙና | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | ናሙና | አማካይ ዉጤት (mean) | መደመኛ ልይይት (Std.) | | | |
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 25 | 27.466 | 2.671 | 25 | 27.426 | 2.993 | 48 | 0.05 | 0.960 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | 25 | 40.306 | 2.264 | 25 | 32.293 | 2.992 | 48 | 10.676 | .000 |

ሠንጠረዥ 9. የሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት "የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር በሚረዱ ብልሃቶችን በመጠቀም ማሰተማር በቅድመ ትምህርትና በድህረ-ትምህርት የፈተናዎች አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ማየት ይቻላል፡፡" መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ-ትምህርቱና በድህረ-ትምህርቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t=10.676 p=.000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ለማስተማር ይረዳል የተባሉትን የማስተማሪያ ስልት ከተማሩ በኋላ  በፊት ከነበራቸው አንብቦ መረዳትና የመጻፍ  ችሎታቸው ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ከዚህም አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ

ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ በማስተማር ከትምህርቱ በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታቸዉ በፊት ከነበራቸው ችሎታ ጉልህ ልዩነት ስላሳየ አወንታዊ መልስ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም "አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በተማሪዎቹ ላይ ምንም ለዉጥ አያመጣም፡፡" የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ተማሪዎቹ በፊት ከነበራቸዉ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ጉልህ ልዩነት በማሳየቱ ዉጤታማነቱ የጎላ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተለዋጭ መላምቱ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ነዉ፡፡

በመሆኑም ዝርዝር ዓላማዎቹም የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል በቅንጅት ማስተማር አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ፋይዳ ለመፈተሽ እና አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር በተማሪዎች ላይ ሊያመጣ የሚችለዉን የችሎታ ልዩነት መመርመር፤ በቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑና ከሙከራ ቡድኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀንጅቶ ማስተማር የተማሪዎቹን ምንባብን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር በሙከራና በቁጥጥር ቡድን የሚካተቱትን የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲወስዱ ተደረጓል፡፡ ባስመዘገቡት ፈተና ዉጤት መሠረት ተቀራራቢ ዉጤት ያስመዘገቡትን ተማሪዎች በመዉሰድና በተራ የናሙና ዘዴ በቡድን በመክፈል ሁለቱም ቡድኖች በቅድመ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን በባዕድ ናሙና ቲ-ቲስት የተገኘውን አማካይ ውጤት (በሠንጠረዥ "1 እና 2" ይመልከቱ)፡፡ እንደ ሠንጠረዡ ዉጤት መሰረት ጥናቱ ከመከናወኑ በፊት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን ሁለቱም ቡድኖች ተቀራራቢ የሆነ ችሎታ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

ከዚያም የቁጥጥር ቡድኑን በነባሩ ዘዴ በመጠቀም የሙከራ ቡድኑን ደግሞ ክሂሎቹን በማቀናጀት ወደ ማስተማር ሥራ ተገብቷል፡፡ በሁለቱም ቡድን እንደየ ማስተማር ስልታቸዉ በመምህራቸዉ ከተማሩ በኋላ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት እንደሚያሳየው በሙከራ ቡድኑ የተሳተፉ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት በቁጥጥር ቡድኑ ካሉ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ በዚህም መሠረት በሁለቱም ቡድኖች መካከል በድህረ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና ጉልህ ልዩነት መኖሩንና የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡(በሠንጠረዥ 3 እና 4ይመልከቱ)፡፡

ይህም የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ የሚለዉን ጥያቄ መልስ ለመመለስ  ከቁጥጥር ቡድኑ ይልቅ የሙከራ ቡድኑ የተሻለ ውጤት ያስመዘገበ ስለሆነ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ፋይዳ እንዳለዉ ማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀናጅቶ ለማስተማር ይረዳሉ የተባሉትን በተለያዩ ምሁራን የተገለጹትን ዘዴዎች በመጠቀም ስለተማሩ ሊሆን ይችላል ብሎ አጥኚዉ ገምቷል፡፡ በመሆኑም የተገኘው ውጤት የሚያሳየው አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በሙከራ ቡድኑ ተሳተፉ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ መሻሻል  በመታየቱ ነዉ፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት የበለጠ ሆኖ በስታትስቲክስ ሲታይ ቲ= 10.676 የp= ዋጋ (.000) ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ሙከራዊ ቡድኑ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የጎላ ልዩነት እንዳለም ያሳያል፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም ግኝት Harpetal(1996)፣ Ruddle (1997) በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ያላቸዉ በመሆኑ  በቅንጅት ቢቀርቡ የአንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ችሎታቸዉ

ከወትሮዉ የበለጠ ሊያሻሻል እንደሚችል በጥናታቸዉ ካረጋገጡት ጋር ተመሳሳይነት አለዉ፡፡ እንዲሁም

ሞገስ (1999) ባደረጉት ጥናት Beerd gew (2003) ዋቢ አድርገዉ እንደገለጹት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለዉ ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምርምሮቹ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክሂሎች መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ይቀራረባል፡፡ በማስከተለም

Little Wood (1981)፡፡ በአሁኑ ወቅት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የተሻለ ዘዴ ነዉ የሚባለዉ ቅንጅታዊ አቀራረብ ሲሆን የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገዉ ደረጃ ግቡን እንዲመታ ያግዛሉ ተብለዉ ከሚጠቀሱት ዉስጥ አንዱ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ነዉ፡፡ ይላሉ በመሆኑም የተገኘዉ ዉጤት ሀሳቡን ይደግፋል፡፡

(Gilbert:1982) በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አላማም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቡ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው ሲሉ Byrne (1981) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

Atkins etal (1996) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግም በተጨማሪ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ይዘቶች በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማስቻልም ነው ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ውጤት ብልጫ እንዲያሳይ ያደረገው ምክንያት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚረዱትን ብልሃቶች ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በትክክል በክፍል ዉሰጥ በመተግበራቸው በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ መሻሻል ማየት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓለማ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ ነዉ፡፡ ዝርዝር ዓላማዎችም አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ፋይዳ  መፈተሽ፤ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል በቅንጅት ማስተማር በተጠኚ ተማሪዎች መካከል ሊያመጣ የሚችለዉን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ልዩነት መመርመር፤ የሚሉትን በተመለከተ  ክሂሎቹን በቅንጅት መማርና  ያለቅንጅት መማር መካከል የታየውን የተማሪዎች የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትናዋል፡፡ እንዲሁም አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ  ማስተማር የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ በፈተና አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ  በባዕድ ናሙና ቲ-ቴሰት ተተንትኗል ፡፡

በዚህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት በመታየቱ የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ዉጤት ምን እንደሚመስል ስመለከት፤ የሙከራ ቡድኑ አማካይ ዉጤት 40.333 የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 32.293 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አማካይ ዉጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ዉጤት በ8.04 በልጦ ተገኝቷል፡፡ ( በሠንጠረዥ 4 ላይ ይመልከቱ)

ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳለዉ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለዉ አስተዋጽዖ ትልቅ እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡

እንዲሁም ከመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች የተገኘዉ ውጤት እንደሚያሳየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለማሳየቱን፤ ነገር ግን በድህረ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት የሙከራ ቡድኑ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱን ማየት ተችሏል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ ክሂሎቹን አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ጠቀሜታ እንዳለው ማወቅ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፎችን" እንደሚባለዉ ምሳሌያዊ ንግግር ሁለቱን ክሂሎች ለየብቻቸዉ ከማስተማር ይልቅ በጥምረት ማስተማር የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታቸዉን በቀላሉ በማሳደግ የክሂሎቹ ተጠቃሚ እንደሚያደርጋቸዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት መፈተሽ፡፡ በሚል ርዕስ በተደረገዉ ጥናት ተሳታፊ የነበሩት የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ አባል ተማሪዎች በሰኮሩ ወረዳ ሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ተሳታፊ የተደረጉ ተማሪዎች 50 ሲሆኑ የተመረጡት በቅድመ ትምህርት ፈተና ተቀራራቢ ዉጤት በማስመዝገባቸዉ ነዉ፡፡ ተጠኚ ተማሪዎችን ተራ የናሙና ዘዴን በመጠቀም በሁለት ቡድን በመመደብ አንድኛዉን ለሙከራ ሌላኛዉን ለቁጥጥር ቡድን እንዲዉሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት በአጭሩ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

በቅድመ ትምህርት ለተማሪዎች ቀርቦላቸዉ በነበረዉ ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ዉጤት 27.426 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አማካይ ዉጤት ደግሞ 27.466 ነዉ፡፡ የ ፒ ዋጋ 0.960 ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ የጉልህነት ደረጃዉን 0.05 ($P<0.05$) የበለጠ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጦዋል፡፡

በመቀጠል በጥናቱ የተሳተፉትን ቡድኖች በተያዘላቸዉ የአራት ሳምንታት የጊዜ ገደብ ዉስጥ ክሂሎቹን በቅንጅት የማስተማሩ ተግባር ከተከናወነ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በድህረ ትምህርት የፈተና ዉጤት መሠረትም የሙከራዉ ቡድን አማካይ 40.306 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 32.293 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የP ዋጋ .000 ሲሆን የጉልህነት ደረጃዉ ($P<0.05$) ያነሰ ነዉ፡፡

ከላይ በድህረ ትምህርት ከቀረበላቸዉ ፈተና ዉጤት በመነሳት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት እንደተከሰተ ማወቅ ይቻላል፡፡ በዚህም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ዉጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡

በመጨረሻም የመላምት ፍተሻ የተካሄደ ሲሆን በሁለቱ ቡድኖች መካከል ከድህረ ትምህርቱ በኋላ የችሎታ መበላለጥ አይታይም የሚለዉ አልቦ መላምት ዉድቅ ሆኖ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ልዩነት ይኖራል የሚለዉ አማራጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

## 5.3. አስተያየት

"የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ" በማስመልከት በሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተካሄደዉ የጥናት ዉጤት በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

- አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ በማዳበር የክሂሉ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸዉ ክሂሎቹን በንጥል ከማስተማር ይልቅ በቅንጅት ቢያስተምሩ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፎችን እንደመምታት ሲለሚቆጠር የተማሪዎቹን የችሎታ ደረጃ ከማሳደጉም በተጨማሪ ለመምህራን ምቹ የመማር ማስተማር አዉድ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ስለዚህ ክሂሎቹን በቅንጅት ቢያስተምሩ፤
- መምህራን የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ ካሉ ምንባቦች ዉጭ የተለያዩ ምንባቦችን ከመጽሐፍት፣ ከመጽሔት፣ ከጋዜጣና ከተለያዩ ጽሁፎች አንብበዉ የተረዱትን ጽፈዉ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያነቡ ቢያደርጉ፤
- በተጨማሪም የተለያዩ ምንባቦችን ከማንበባቸው በፊት የምንባቡን ርዕስ አይተው የቀደሙ እውቀታቸውን የመቀስቀስ ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን እንዲያዘጋጁና ዓላማ ወስነው እንዲያነቡ ዘወትር ቢያነቃቁ፤
- የትምህርት ቤቱ የስነ-ጽሑፍ፣ የድራማ፣ የሚኒ ሚዲያ ክበብ ተጠሪዎች ተማሪዎችን በነዚህ ክበባት እንዲመዘገቡ ቢያደርጉና የተዘመገቡ አባላትም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከተለያዩ መጽሐፍትና መጽሔቶች አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ አጠናቅረዉ በየጊዜው በሰንደቅ ዓላማ እና በዕረፍት ሠዓታቸዉ በንባብ እንዲያቀርቡ ቢያደርጉ፤
- የመጽሐፍ አዘጋጆች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግና ተማሪዎችን ዉጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፎች ዉስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ አድርገዉ ቢያዘጋጁ፤

## ዋቢ ጽሑፎች

ማረው አለሙ፡፡ (1998)፡፡ **የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡** አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማስተዋል ውበቱ፡፡ (1989)፡፡ "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር፡፡ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ሞገስ አመራ:: (1999)፡፡የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፡፡ ለድህረምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ፣ (ያልታተመ)፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1991)፡፡ "ንባብን አንብቦ መረዳትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ፡፡ "አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋ ጥናት ተቋም ለ10ኛ አመት የቋንቋ ጥናት ስንፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡

አለም እሸቱና ጽጌ አበበ (1997)፡፡ **አማርኛ የመምህሩ መምሪያ 9ኛ ክፍል፡፡** አዲስ አበባ ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት ( ተሻሽሎ የወጣ)፡፡

አታኽልቲ መኮንን፡፡ (1998)፡፡ "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ዘዴ አተገባበር ፍተሻ"፡፡ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ (ያልታተመ) ፡፡

እመቤት እሸቴ፡፡ (2011)፡፡ አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ (ያልታተመ)፡፡

እሸቴ መብራት፡፡ (2003)፡፡ "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት"፡፡ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998)፡፡ **የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡** አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Atkin S, J.etal. (1996). **Skills development methodology** part two Addis Ababa: Addis Ababa Universty press.

Barrs, Myra. (2000). **The Reader in the Writer.Reading** ( United Kingdom Reading Association),

Best, J.W and Khan, J.V. (1993). **Reaserch in education** . Needham heights,

Block, Cand Mangieri,J.(1995). **Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature**, Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion

Block, Cathy Colling. (1997). **Teaching the Language arts. Expanding thinking Student Centered instraction.** Bastone: Allyn and Bacon

Burgss, R.G. (Ed). (1989) **strategies of Educational Research: Qualitative Method**. London and Philade/Phia: The Falmer Press.

Byrne, D. (1991). **Teaching Writing Skills.** London: Longman Group, UK limited.

Byrne, D. (1981). **Integration Skill** in Johnson and Marrow.HongKong: Long man Group Ltd.

Celce-Murcia, M. (eds.) (1991). **Teaching English as a Second or Foreign Language.** (2nd ed.). Boston: Heinl & Heinle publishers.Ltd

Conley, Mark W. (1997). **Reading and Writing**: teaching for the connection. (2nd ed.)less har court Bracheand company.

Gary, cobine. (1995). **Writing as a response to reading.**

Gilbert, J (1982). **Clear Speech: pronounciation and listening compheration in English.**TesolQuarterly Vol 25 N01 (spring ,1991) pp.51-75.

Grellet, J. (1981). **Developing Reading Skills.** Cambridge: Cambridge: University Press.

Harmer,J. (1991). **The practice of English language Teaching.** London: New York long man.

Harp, Bill and Brewry, John.(1996). **Reading and writing Teaching for the connection.** (2nd ed.)S.A: Har court brace and campany.

Heaton, J.D. (1988). **Writing English Language Tests.** (2nd Ed). London: Longman. Publishers limited.

Hughes, D.M. (1997) **A Longitudinal Study of the Development of Writing** in 4-7 Year Old Children. University of Reading, PhD thesis. Unpublished

Koul, C. (1996). **Methodology of Educational Research.** (2nd Revised Ed). New Delh: Hindustan Offset Printers

Littile wood, W. (1981). **Communcative language teaching.**Cambridge:Cambridg Unverstiy press

Mc Donough, J. and Shaw, C. (1992). **Integrated Skills. ELT a teachers guide.** Oxford: Black Well.

May, Frank B.(1990). **Reading as communication.**New york: Macmilan Publishing company.

Norman, K .and Yuvona, S .(1994) **Handbook of Qualitative Research.** London: Sage Publications

Oxford, R. (2001). **Integrated Skills in the ELS/EFL Class room.** ERTV. Maio:eric@Cas.org.

Raimes, A. (1983). **Techniques in teaching writing.** Oxford: Oxford University press Inc.

Rivers, W. (1981).**Teaching Foreign Langage Skills.**Chicago:Cicago University Press.

Ruddel, Martha Rapp (1997). **Teaching content Reading and Writing.** (2nd.ed.). U.A.S: Allyn and Bacon.

Shanehan. T. (2006). **The National Reading Panal.** Report Practical Advice for Teachers Learning Point Associates. Chicago.

Smith, F. (1985). Reading. Great Britain Cambridge University presses (2nd ed.)Less har court Brache and company.

Widdowson, H. G. (1978). **Teaching Language as Communication.**Oford: oup

Williams, (ed.) (1984). **Reading in the Language Class room** .London: Macmillan Publishers Ltd.

Ur. P.(2006). **A course in language Teaching Practice and Theory.** 13th Printing Cambridge: Cambridge University.

# አባሪዎች

## አባሪ “ 1 ”

## አጠቃላይ ለተጠኚ ተማሪዎች የተሰጠ የቅድመ ችሎታ ፈተና ዉጤት

| ተራ ቁጥር | በሶስት መምህራን ታርሞ የተሰጠ የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት (60%) | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሦስት | አማካይ ዉጤት |
| 1 | 26 | 30 | 29 | 28.33333 |
| 2 | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 3 | 33 | 32 | 30 | 31.66667 |
| 4 | 18 | 16 | 15 | 16.33333 |
| 5 | 14 | 13 | 14 | 13.66667 |
| 6 | 23 | 18 | 17 | 19.33333 |
| 7 | 21 | 17 | 12 | 16.66667 |
| 8 | 21 | 17 | 18 | 18.66667 |
| 9 | 20 | 17 | 16 | 17.66667 |
| 10 | 17 | 16 | 15 | 16 |
| 11 | 17 | 16 | 15 | 16 |
| 12 | 17 | 16 | 15 | 16 |
| 13 | 30 | 28 | 28 | 28.66667 |
| 14 | 28 | 27 | 29 | 28 |
| 15 | 23 | 26 | 28 | 25.66667 |
| 16 | 25 | 28 | 24 | 25.66667 |
| 17 | 26 | 28 | 29 | 27.66667 |
| 18 | 25 | 27 | 29 | 27 |
| 19 | 27 | 29 | 31 | 29 |
| 20 | 23 | 27 | 26 | 25.33333 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 21 | 20 | 23 | 25 | 22.66667 |
| 22 | 13 | 12 | 14 | 13 |
| 23 | 14 | 15 | 16 | 15 |
| 24 | 16 | 18 | 19 | 17.66667 |
| 25 | 18 | 16 | 13 | 15.66667 |
| 26 | 18 | 16 | 13 | 15.66667 |
| 27 | 16 | 15 | 15 | 15.33333 |
| 28 | 14 | 13 | 17 | 14.66667 |
| 29 | 17 | 14 | 17 | 16 |
| 30 | 13 | 16 | 19 | 16 |
| 31 | 15 | 11 | 14 | 13.33333 |
| 32 | 12 | 12 | 17 | 13.66667 |
| 33 | 11 | 13 | 12 | 12 |
| 34 | 13 | 12 | 14 | 13 |
| 35 | 14 | 15 | 16 | 15 |
| 36 | 16 | 18 | 19 | 17.66667 |
| 37 | 18 | 16 | 13 | 15.66667 |
| 38 | 22 | 24 | 26 | 24 |
| 39 | 25 | 27 | 27 | 26.33333 |
| 40 | 33 | 31 | 30 | 31.33333 |
| 41 | 31 | 32 | 33 | 32 |
| 42 | 17 | 18 | 15 | 16.66667 |
| 43 | 13 | 15 | 12 | 13.33333 |
| 44 | 15 | 13 | 11 | 13 |
| 45 | 21 | 19 | 14 | 18 |
| 46 | 28 | 27 | 26 | 27 |
| 47 | 25 | 26 | 24 | 25 |
| 48 | 33 | 31 | 30 | 31.33333 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 49 | 14 | 12 | 19 | 15 |
| 50 | 16 | 15 | 14 | 15 |
| 51 | 31 | 30 | 29 | 30 |
| 52 | 25 | 28 | 27 | 26.66667 |
| 53 | 26 | 28 | 26 | 26.66667 |
| 54 | 26 | 24 | 22 | 24 |
| 55 | 20 | 22 | 21 | 21 |
| 56 | 24 | 21 | 23 | 22.66667 |
| 57 | 31 | 29 | 27 | 29 |
| 58 | 17 | 16 | 17 | 16.66667 |
| 59 | 25 | 26 | 27 | 26 |
| 60 | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 61 | 17 | 18 | 14 | 16.33333 |
| 62 | 13 | 11 | 13 | 12.33333 |
| 63 | 28 | 28 | 26 | 27.33333 |
| 64 | 27 | 26 | 28 | 27 |
| 65 | 29 | 26 | 28 | 27.66667 |
| 66 | 15 | 16 | 14 | 15 |
| 67 | 27 | 26 | 28 | 27 |
| 68 | 31 | 29 | 27 | 29 |
| 69 | 12 | 13 | 18 | 14.33333 |
| 70 | 32 | 31 | 30 | 31 |
| 71 | 31 | 29 | 30 | 30 |
| 72 | 31 | 33 | 30 | 31.33333 |
| 73 | 22 | 24 | 25 | 23.66667 |
| 74 | 14 | 16 | 16 | 15.33333 |
| 75 | 18 | 15 | 15 | 16 |
| 76 | 25 | 23 | 24 | 24 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 77 | 22 | 17 | 15 | 18 |
| 78 | 13 | 11 | 14 | 12.66667 |
| 79 | 22 | 18 | 11 | 17 |
| 80 | 21 | 19 | 17 | 19 |
| 81 | 19 | 17 | 13 | 16.33333 |
| 82 | 18 | 17 | 16 | 17 |
| 83 | 16 | 12 | 18 | 15.33333 |
| 84 | 18 | 17 | 14 | 16.33333 |
| 85 | 19 | 16 | 15 | 16.66667 |
| 86 | 16 | 13 | 16 | 15 |
| 87 | 13 | 14 | 15 | 14 |
| 88 | 16 | 17 | 12 | 15 |
| 89 | 19 | 16 | 15 | 16.66667 |
| 90 | 16 | 15 | 13 | 14.66667 |
| 91 | 22 | 24 | 20 | 22 |
| 92 | 16 | 14 | 18 | 16 |
| 93 | 30 | 27 | 29 | 28.66667 |
| 94 | 12 | 15 | 17 | 14.66667 |
| 95 | 24 | 28 | 27 | 26.33333 |
| 96 | 17 | 16 | 15 | 16 |
| 97 | 18 | 17 | 16 | 17 |
| 98 | 22 | 16 | 14 | 17.33333 |
| 99 | 30 | 31 | 29 | 30 |
| 100 | 28 | 29 | 30 | 29 |
| 101 | 16 | 18 | 16 | 16.66667 |
| 102 | 11 | 14 | 19 | 14.66667 |
| 103 | 15 | 15 | 13 | 14.33333 |
| 104 | 31 | 30 | 30 | 30.33333 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 105 | 16 | 16 | 13 | 15 |
| 106 | 19 | 15 | 15 | 16.33333 |
| 107 | 14 | 12 | 17 | 14.33333 |
| 108 | 22 | 26 | 28 | 25.33333 |
| 109 | 19 | 17 | 18 | 18 |
| 110 | 30 | 29 | 31 | 30 |
| 111 | 25 | 24 | 25 | 24.66667 |
| 112 | 13 | 14 | 15 | 14 |
| 113 | 30 | 30 | 31 | 30.33333 |
| 114 | 19 | 18 | 16 | 17.66667 |
| 115 | 14 | 12 | 15 | 13.66667 |
| 116 | 21 | 18 | 16 | 18.33333 |
| 117 | 19 | 18 | 12 | 16.33333 |
| 118 | 29 | 28 | 30 | 29 |
| 119 | 24 | 26 | 24 | 24.66667 |
| 120 | 19 | 15 | 16 | 16.66667 |

## አባሪ “ 2 ”

### የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት መግለጫ

| ተራ ቁጥር | በሶስት መምህራን ታርሞ የተሰጠ የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት (60%) | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሦስት | አማካይ ዉጤት |
| 01B | 30 | 28 | 28 | 28.66667 |
| 02B | 28 | 27 | 29 | 28 |
| 03B | 23 | 26 | 28 | 25.66667 |
| 04B | 25 | 28 | 24 | 25.66667 |
| 05B | 26 | 28 | 29 | 27.66667 |
| 06B | 25 | 27 | 29 | 27 |
| 07B | 27 | 29 | 31 | 29 |
| 08B | 23 | 27 | 26 | 25.33333 |
| 09B | 20 | 23 | 25 | 22.66667 |
| 10B | 31 | 30 | 30 | 30.33333 |
| 11B | 30 | 30 | 31 | 30.33333 |
| 12B | 24 | 28 | 27 | 26.33333 |
| 13B | 26 | 30 | 29 | 28.33333 |
| 14B | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 15B | 33 | 32 | 30 | 31.66667 |
| 16B | 28 | 27 | 26 | 27 |
| 17B | 25 | 26 | 24 | 25 |
| 18B | 33 | 31 | 30 | 31.33333 |
| 19B | 30 | 27 | 29 | 28.66667 |
| 20B | 29 | 28 | 30 | 29 |
| 21B | 31 | 30 | 29 | 30 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22B | 25 | 28 | 27 | 26.66667 |
| 23B | 26 | 28 | 26 | 26.66667 |
| 24B | 26 | 24 | 22 | 24 |
| 25B | 20 | 22 | 21 | 21 |
| 26I | 24 | 21 | 23 | 22.66667 |
| 27I | 31 | 29 | 27 | 29 |
| 28I | 22 | 24 | 20 | 22 |
| 29I | 25 | 26 | 27 | 26 |
| 30I | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 31I | 30 | 29 | 31 | 30 |
| 32I | 25 | 24 | 25 | 24.66667 |
| 33I | 28 | 28 | 26 | 27.33333 |
| 34I | 27 | 26 | 28 | 27 |
| 35I | 29 | 26 | 28 | 27.66667 |
| 36I | 22 | 26 | 28 | 25.33333 |
| 37I | 27 | 26 | 28 | 27 |
| 38I | 31 | 29 | 27 | 29 |
| 39I | 24 | 26 | 24 | 24.66667 |
| 40I | 32 | 31 | 30 | 31 |
| 41I | 31 | 29 | 30 | 30 |
| 42I | 31 | 33 | 30 | 31.33333 |
| 43I | 22 | 24 | 25 | 23.66667 |
| 44I | 30 | 31 | 29 | 30 |
| 45I | 28 | 29 | 30 | 29 |
| 45I | 25 | 23 | 24 | 24 |
| 47I | 33 | 31 | 30 | 31.33333 |
| 48I | 31 | 32 | 33 | 32 |
| 49I | 22 | 24 | 26 | 24 |
| 50I | 25 | 27 | 27 | 26.33333 |

# አባሪ “ 3 ”

## የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ- ትምህርት ፈተና ዉጤት (60%)

| ተ.ቁጥር | የሙከራ ቡድን | ተ.ቁጥር | የቁጥጥር ቡድን |
|---|---|---|---|
| 1 | 28.66667 | 1 | 22.66667 |
| 2 | 28 | 2 | 29 |
| 3 | 25.66667 | 3 | 22 |
| 4 | 25.66667 | 4 | 26 |
| 5 | 27.66667 | 5 | 30.66667 |
| 6 | 27 | 6 | 30 |
| 7 | 29 | 7 | 24.66667 |
| 8 | 25.33333 | 8 | 27.33333 |
| 9 | 22.66667 | 9 | 27 |
| 10 | 30.33333 | 10 | 27.66667 |
| 11 | 30.33333 | 11 | 25.33333 |
| 12 | 26.33333 | 12 | 27 |
| 13 | 28.33333 | 13 | 29 |
| 14 | 30.66667 | 14 | 24.66667 |
| 15 | 31.66667 | 15 | 31 |
| 16 | 27 | 16 | 30 |
| 17 | 25 | 17 | 31.33333 |
| 18 | 31.33333 | 18 | 23.66667 |
| 19 | 28.66667 | 19 | 30 |
| 20 | 29 | 20 | 29 |
| 21 | 30 | 21 | 24 |
| 22 | 26.66667 | 22 | 31.33333 |
| 23 | 26.66667 | 23 | 32 |
| 24 | 24 | 24 | 24 |
| 25 | 21 | 25 | 26.33333 |

## አባሪ “ 4 ”

## የሙከራዉና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት መግለጫ(60%)

| ተራ ቁጥር | በሶስት መምህራን ታርሞ የተሰጠ የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት (60%) | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አራሚ አንድ | አራሚ ሁለት | አራሚ ሦስት | አማካይ ዉጤት |
| 01B | 38 | 40 | 43 | 40.33333 |
| 02B | 40 | 42 | 44 | 42 |
| 03B | 38 | 41 | 43 | 40.66667 |
| 04B | 35 | 39 | 40 | 38 |
| 05B | 40 | 42 | 44 | 42 |
| 06B | 41 | 43 | 41 | 41.66667 |
| 07B | 45 | 44 | 45 | 44.66667 |
| 08B | 35 | 38 | 39 | 37.33333 |
| 09B | 36 | 39 | 38 | 37.66667 |
| 10B | 41 | 42 | 41 | 41.33333 |
| 11B | 43 | 44 | 45 | 44 |
| 12B | 35 | 38 | 37 | 36.66667 |
| 13B | 37 | 36 | 38 | 37 |
| 14B | 39 | 38 | 40 | 39 |
| 15B | 41 | 43 | 41 | 41.66667 |
| 16B | 36 | 38 | 39 | 37.66667 |
| 17B | 44 | 43 | 41 | 42.66667 |
| 18B | 38 | 40 | 41 | 39.66667 |
| 19B | 39 | 41 | 39 | 39.66667 |
| 20B | 41 | 40 | 40 | 40.33333 |
| 21B | 43 | 42 | 41 | 42 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22B | 36 | 38 | 37 | 37 |
| 23B | 41 | 43 | 43 | 42.33333 |
| 24B | 41 | 42 | 41 | 41.33333 |
| 25B | 42 | 41 | 40 | 41 |
| 26I | 33 | 32 | 33 | 32.66667 |
| 27I | 35 | 37 | 34 | 35.33333 |
| 28I | 33 | 36 | 36 | 35 |
| 29I | 34 | 37 | 38 | 36.33333 |
| 30I | 35 | 36 | 34 | 35 |
| 31I | 32 | 31 | 32 | 31.66667 |
| 32I | 35 | 34 | 35 | 34.66667 |
| 33I | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 34I | 38 | 40 | 43 | 40.33333 |
| 35I | 34 | 32 | 32 | 32.66667 |
| 36I | 30 | 29 | 30 | 29.66667 |
| 37I | 30 | 31 | 30 | 30.33333 |
| 38I | 28 | 30 | 27 | 28.33333 |
| 39I | 32 | 31 | 29 | 30.66667 |
| 40I | 30 | 33 | 35 | 32.66667 |
| 41I | 32 | 31 | 30 | 31 |
| 42I | 30 | 32 | 30 | 30.66667 |
| 43I | 31 | 30 | 31 | 30.66667 |
| 44I | 32 | 33 | 33 | 32.66667 |
| 45I | 35 | 36 | 38 | 36.33333 |
| 45I | 28 | 26 | 25 | 26.33333 |
| 47I | 32 | 31 | 32 | 31.66667 |
| 48I | 30 | 33 | 33 | 32 |
| 49I | 28 | 29 | 30 | 29 |
| 50I | 31 | 32 | 30 | 31 |

## አባሪ “5 ”

## የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ- ትምህርት ፈተና ዉጤት (60%)

| ተ.ቁጥር | የሙከራ ቡድን | ተ.ቁጥር | የቁጥጥር ቡድን |
|---|---|---|---|
| 1 | 40.33333 | 1 | 32.66667 |
| 2 | 42 | 2 | 35.33333 |
| 3 | 40.66667 | 3 | 35 |
| 4 | 38 | 4 | 36.33333 |
| 5 | 42 | 5 | 35 |
| 6 | 41.66667 | 6 | 31.66667 |
| 7 | 44.66667 | 7 | 34.66667 |
| 8 | 37.33333 | 8 | 30.66667 |
| 9 | 37.66667 | 9 | 40.33333 |
| 10 | 41.33333 | 10 | 32.66667 |
| 11 | 44 | 11 | 29.66667 |
| 12 | 36.66667 | 12 | 30.33333 |
| 13 | 37 | 13 | 28.33333 |
| 14 | 39 | 14 | 30.66667 |
| 15 | 41.66667 | 15 | 32.66667 |
| 16 | 37.66667 | 16 | 31 |
| 17 | 42.66667 | 17 | 30.66667 |
| 18 | 39.66667 | 18 | 30.66667 |
| 19 | 39.66667 | 19 | 32.66667 |
| 20 | 40.33333 | 20 | 36.33333 |
| 21 | 42 | 21 | 26.33333 |
| 22 | 37 | 22 | 31.66667 |
| 23 | 42.33333 | 23 | 32 |
| 24 | 41.33333 | 24 | 29 |
| 25 | 41 | 25 | 31 |

# አባሪ " 6 "

## ቅድመ ትምህርት ፈተና

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

ኮድ -----

ለሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ

ቅድመ ትምህርት ፈተና (ከ60%)

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ1፡00 ሰዓት

**_አጠቃላይ መመሪያ_**

ውድ ተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ "የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው፡፡

የመጀመሪያው ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ የሚመልሱና የምንባቡን ታሪክ በአንድ አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ የሚያዝ ጥያቄ ሲሆን፤ ሁለተኛዉ የቀረበላቸዉን ምንባብ በማንበብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀጽ አሳጥረዉ የሚያዝ ጥያቄዎችን ይዟል።

**_ምንባብ_**

ያለ ምንም ጉርምርምታ ጸጥ ብሎና የሰላማዊነትን ግርማ ሞገስ ተጎናጽፎ ከሚንቀዠቀዠዉ ዝናብ ለማምለጥ በየቤቱ ጥግ የተጠለለዉ መንገደኛ ወጨፎና ወጀብ ባለመኖሩ ዘና ብሎ ቆሟል፡፡ ከዝናቡ ጋር ፉክክር የያዙ የሚመስሉ መንገደኞችም ልብሳቸዉን ሰብሰብ አደርገዉ ሲሮጡ አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡

ዕዉሩ ለማኝ አባ አያሌዉ አኩፋዳቸዉን አቅፈዉ፣ ድሪቷቸዉን እስከ ቅንድባቸዉ ተከናንበዉ፣ ጭብጥ ብለዉ ተቀምጠዉ አንጀት በሚላ እንጉርጉሯቸዉን ሲያስኾጎደጉዱት ረጋ ካለዉ የዝናቡ

አወራረድ ጋር ተቀናብሮ እልም ካለ የሃሳብ ዱር ይጨምራል፡፡ ያለፈዉ ህይወታቸዉ ትዝታ ጓዙን ጠቅልሎ ማንሠበብ የሚጀምረዉ ዝናቡ ሊመጣ ማጉረምረም ሲጀምር ነዉ፡፡ አንድ ጊዜ መዝፈን ከጀመሩ ደግሞ ግጥም አያልቅባቸዉም፡፡ ጉሮሯቸዉ አይሻክርባቸዉም፡፡ ያሳለፉት የህይወት ዘመን በግጥም እየተንዶለዶለ የሚፈስላቸዉ እንጂ በሽማግሌ ጭንቅላታቸዉ ተቀነባብሮ የሚቀርብ አይደለም፡፡

እንጉርጉሯቸዉ ልቤን ሰለቦኝ ስለ እናታቸዉ፣ ስለቤተሰባቸዉና ስለሃገራቸዉ፣ ስለወንዙ፣ ስለዱሩ ሲያንጎራጉሩ የወላጆቼ ቤት አፈር ፊጭቼ፣ ዉሃ ቀድቼ ያደግሁበት ባዕድ ሰዉ የሌለበት ሠፈሬ ፣ ወንዙ፣ ዱሩ በዓይን ህልናዬ ሲያንሠብብኝ፤ ዜማቸዉን ቀየር ያደርጉና ስለ ከንፈር ወዳጅ፣ ስለ ልጅነት ፍቅር ሲያሽጎደጉዱት እንደገና ልቤን እንደ ቦይ ዉሃ ነድተዉ ከፍቅር ዓለም ዉስጥ አስገቡኝ፡፡

*የዝና ወርቁና ጀማል ሱሌይማን ፤ያልተሸጠዉ ሴይጣን ፤ገጽ ፤128-129*

***መመሪያ አንድ፡-*** <u>**በምንባቡ መሠረት ለጥያቄዎቹ ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጭ፡፡ (45%)**</u>

1. በምንባቡ ዉስጥ የተገለጸዉ የዝናብ ሁኔታ የሚመለክተዉ በስንተኛዉ አንቀጽ በየትኛዉ ሀረግ ነው? (2%)

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

2. በምንባቡ ዉስጥ ከዝናቡ ጋር ፉክክር የያዙት የተባሉት እነማን ናቸዉ? ለምን ይመስላችኋል? በዝርዝር ግለጽ/ጭ/፡፡ (5%)

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------------

   ------------------------------------------------------------------------------------------

3. የአባ አያሌዉ አካላዊ ገጽታ ምን ይመስላል? ተቀምጠዉ የሚያንጎራጉሩት የት ቦታ ነዉ? (5%)

___

4. በምንባቡ ዉስጥ "**ልቤን ሰልቦኝ**" የሚለዉና "**ልቤን እንደ ቦይ ዉሃ ነድተዉ**" የሚሉት ሁለት ሀረጎች ምን ለማለት ይመስላችኋል? ዘርዘር አድርገህ/ሽ/ ጻፍ/ፊ/፡፡(5%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------

5. በምንባቡ ዉስጥ ያሉት ገጸ-ባህሪያት ስንት ናቸዉ ተግባራቸዉን ዘርዘር አድርገህ/ሽ/ ጻፍ/ፊ/፡፡ (5%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------

6. በምንባቡ ውስጥ በምናብህ /ሽ/ የተከሰቱት ነገሮች ምን ምን ናቸው? በቅድመ ተከተል በዝርዝር ጻፍ/ፊ/፡፡(10%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------

7. አጠቃላይ የምንባቡን ታሪክ በአንድ አንቀጽ አሳጥረህ ጻፍ/ፊ፡፡ (10%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------

8. የምንባቡ ድርሰት ተደራጅቶ የቀረበበትን የአጻጻፍ ስልት ግለጽ /ጭ/፡፡ (2%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------

**መመሪያ ሁለት፡-የሚከተለውን ምንባብ በማንበብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀፅ ፃፉ፡፡(15%)**

አሮጌዉና አዲሱ ትዉልድ የሚባል ነገር ሊሰማን አይገባም፡፡ አሮጌ የሚሰበር ነዉ፣ አዲሱም ያልተሟሸ ሸክላ ነዉ፣ እኛ ግን እንዲህ አይደለንም፣ ወይፈኖች የሚገሩት በበሬ ነዉ፣ ስለዚህ አጥማጅና መቀናጆ ለአንድ ፊር ሞፊር መነተት አለባቸዉ፡፡

ኢትዮጵያ ትደግ፣ ወገኖቻችን ይበልጽጉ፣ በዚህ ዓላማ በዚህ መንፈስ በዚህ ፍቅር የምንመራ ስንሆን የፋንታን ክፍያ ትተን ለሚፈለገዉ ግብ የሚፈለገዉን ማድረግ ነዉ፡፡ የዛሬዎቹ እንደ ትናንትና እንሆናለን፣በዛሬዎቹም ላይ የትናንትናዎቹ አሉ፣ አዎቀ በመናደድ ሀገር አትበለጽግም፣ በመሮጥ መዉደቅ አለበት፣ በመቀመጥም በሽታ አለ፡፡

ከአቅም በላይ ሳንሮጥ መቀመጥም ሳናዛ እነዳቅማችን እንደመጠናችን መጓዝ ሳይሆን መገስገስ ይኖርብናል፡፡የባልና የሚስቶች መኳረፍ ለሥራ ቤት ይበጃል ይባላል፣ የኛ ተባሮ ያለመሥራትም ለአንዳንድ ጩልሌ ያመች ይሆናል ፡፡

ሁሉን ነገር መጥፎ ካላደረግነዉ መጥፎ የለም፡፡ሳንቀምሰዉ ማርን ልናመረዉ እንችላለን፡፡ ያ አለማችን ሊሆን አይገባም፣ ለአንድ ሐገር ከርስ የምንሰራዉ የአንድ አካል ቅጥልጥል ብልቶች መሆን ይገባናል፡፡

/ጳዉሎስ ኞኞ  አንድነት ለአንድ ዓለማ እንሰለፍ የኢትዮጵያ ድምጽ ግንቦት 3 ቀን 1955 ዓ.ም /

# አባሪ "7 "

## ድህረ-ትምህርት ፈተና

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

ኮድ -----

ለሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ

ድህረ አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፈተና (ከ60%)

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ1፡00 ሰዓት

**<u>አጠቃላይ መመሪያ</u>**

ውድ ተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ "የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው፡፡

የመጀመሪያው ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ የሚመልሱና የምንባቡን ታሪክ በአንድ አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ የሚያዝ ጥያቄ ሲሆን ፤ ሁለተኛዉ የቀረበላቸዉን ምንባብ በማንበብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀጽ አሳጥረዉ የሚጻፍ የሚያዝ ጥያቄዎችን ይዟል።

**<u>ምንባብ</u>**

ትዕግስት ባስራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝ ውብ ልጃገረድ ነች፡፡ እንደሀር ነዶ እየተዘናፈለ ወርዶ ዳሌዋን የሚዳስሰው ፀጉሯ የውበቷ ሰገነት ነው፡፡ አይኗ ከብር አሎሎ ይፎካከራል፡፡ መልከትከት ስትል እንደ ፈርጥ ይንቦገቦጋል፤ በሰው ስሜት ውስጥ ሰርጎ የመግባትና የማደንዘዝ ሀይል ያለው መልዕክትም ያስተላልፋል፡፡

ሽፍሽፍቷ እንደበልግ ሳር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስላል፡፡ ጆሮዋ ላይ ያንጠለጠለችው የሕፃን ልጅ አምባር የሚያካክሉት ጉትቻዎቿ የፀሐዩን ጨረር ተቀብለው ሲያንፀባርቁ በውበት ላይ ውበት ይጨምሩለታል፡፡ ሰልፉ እንዳማረላቸው ወታደሮች ችምችም ብለው የበቀሉት ጥርሶቿ ሃጫ በረዶ ይመስሉ፡፡ ምንግዜም በሳቀች የምትባል ዓይነት ነች፡፡ የበሰለ ብርቱካን በሚመስለው ጉንጪ ላይ የሚዘዋወረው ደሟ ቢነኳት የምትሳሳ አድርጓታል፡፡ የደም ገንቦ ነች፡፡

ፊገግ ስትል በግራ ጉንጪ ላይ ብቅ የሚለው ስርጉዳት ሌላው ማራኪ ተፈጥሮዋ ነው፡፡ አይኖቿን አማክሎ ቀጥ ብሎ የወረደው አፍንጫዋም የፊቷን ፀዳል ከወራሪ ለመጠበቅ የቆመ ሰይፍ ይመስላል፡፡ ደረቷ ባለሙያ አናጢ የጠረበው ሳንቃ ይመስላል፡፡ ግራና ቀኝ እንደቆሙ ቃፊሮች ደረቷ ላይ የበቀሉት አጎጠጎጤዎቿም የለበሰችውን ስስ ሹራብ ነድለው ለመውጣት የሚታገሉ ይመስላሉ፡፡ የአረማመዷን ስልት ተከትለው ስለሚንቀሳቀሱ የወጣቶችን ቀርቶ የእድሜ ጠገቦችንም ሰርቀው ያስቀራሉ፡፡ የሽንጧ ቅጥነት ከንብ አውራ ጋር ያመሳስላታል፡፡ ችቦ አይሞላም ወገቧ የሚባልላት አይነት ነች፡፡ ኮራ ያለው ዳሌዋ ሀረጉን ሽንጧን አቅፎ ደግፎ የያዘው ፅኑ መሰረት ነው፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ከምንባቡ ለወጡት ሀረጋት የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በጽሁፍ ግለጽ/ጪ (6%)***

1. “የውበቷ ሰገነት” (2%) ------------------------------------------------------------------------

2. “አይኗ ከብር አሎሎ” ይፎካከራል፡፡ (2%) --------------------------------------------------

3. “የደም ገንቦ” (2%) ----------------------------------------------------------------------------

4. የህይወትን አካላዊ ገጽታ ዘርዘር አድርገህ/ሽ/ ጻፍ/ፊ/፡፡ (10%)

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------

5. በምንባቡ ዉስጥ ስንት ገጸ-ባህሪያት አሉ? ባህሪያቸዉስ? ዘርዘር አድርገህ/ሽ/ ጻፍ/ፊ/፡፡ (6%)

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

6. በምንባቡ ውስጥ በምናብህ/ሽ/ የተከሰቱት ነገሮች ምን ምን ናቸው? በቅድመ ተከተል በዝርዝር ጻፍ/ፊ/፡፡(10%)

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------

7. አጠቀላይ የምንባቡን ታሪክ በአንድ አንቀጽ አሳጥረህ ጻፍ/ፊ፡፡ (10%)

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

የምንባቡ ድርሰት ተደራጅቶ የቀረበበትን የአጻጻፍ ስልት ግለጽ /ጭ/፡፡ (2%)

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሁለት፡-የሚከተለውን ምንባብ በማንበብ የሀሳብ ፍሰቱን በመጠበቅ በሁለት አንቀፅ ፃፉ*** (15%)

ኢትዮጵያ በብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች የተደነቀ ረጅምና አኩሪ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡ ታዋቂነት ያላት ሀገራችን በዘመናት ታሪኳ ዉስጥብዙ ዉጣ ዉረድና ፈተና ደርሶባታል፡፡ ይሁን እንጂ በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ያልተቋረጠ ተጋድሎ ህልዉናዋ ተጠብቆ ኖሯል፡፡

በጀግንነትና በመስዋዕትነት ያጌጠዉ የኢትዮጵያ የነጻነት ታሪክ ተከብሮ መኖር ሲወሳ ምን ጊዜም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ሁኔታዉ የዕድል ወይም የአጋጣሚ ሳይሆን የሰፊዉ ህዝብ ጀግንነትና መስዋዕትነት ዉጤት መሆኑ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያ በረጅሙ ታሪኳ ዉስጥ ያለፈችባቸዉ በረጅሙ ተጋሎ የተሞሉ ትግሎች ሁሉ ነጻነቷንና ሉዓላዊነቷን ለመጠበቅ እንጂ የሌሎችን ግዛትና አንድነት ለመድፈር አይደለም፡፡

ሀገራችንን የጠላቶቿ የትኩረት ዓላማ ካደረጓት ልዩልዩ ምክንያቶች መካከል አንዱ የተፈጥሮ ሀብቷና ዉበቷ ሲሆኑ ሌላዉ ደግሞ የምትገኝበት አከባቢ ስትራቴጃዊነት ነዉ ፡፡ ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆ መካከል ቁልፍ ሥፍራ ይዛ ትገኛለች፡፡ የዉጭ ሀይሎች ያለማቋረጥ ሲነሱብን የኖሩትም ይህን አንዱን መሠረታዊ ሁኔታ ምክንያት በማድረግና ለመቆጣጠር በመፈለግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ለሀገራችን ያለንን እጅግ ጥልቅ ፍቅር ምርኩዝ በማድረግ የዉጭ ሀይሎችን ያልተቋረጠ ጠላትነትና ወረራ ተቋቁመናል፡፡የተሰነዘሩብን ተደጋጋሚ ጥቃቶች የቁጭትና የአትንኩኝነት መንፈሳችንን አጠንክሩት እንጂ እንድንበገር አላደረጉንም፡፡ ለዚህም በተደጋጋሚ የተቀዳጀናቸዉ ድሎች ምስክሮች ናቸዉ፡፡ ከሁለት ምዕተ-ዓመት በፊት ካፒታሊዝም በአዉሮፓ ዳብሮ ሌሎች ሀገሮችን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት በጠነከረ መንገድ ተንቀሳቅሶ በተለይም በአፍሪካን ኢላማዉ አድርጎ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያ ለቅኝ ግዛትነት ከተተኮረችባቸዉ ሀገሮች አንዷ ነበረች ፡፡

እ.አ.አ.በ1869 የስዊዝ ቦይ መከፈት የቀይ ባህር አከባቢን ጠቀሜታ ስላጎላዉ የወቅቱን ሀያላን መንግስታት ትኩረት ስቧል፡፡ ያ የታሪክ ወቅት በዘመነ መሳንፍት ተዳክሞ የነበረዉን የኢትዮጵያ መንግስት የማማከል ሂደት በአጼ ዮሐንስ የጠነከረበት ነበር፡፡ ይህም የማዕከላዊ መንግስት እየጠነከረ መምጣት በተደጋጋሚ የተሰነዘሩትን ጥቃቶች ለመከላከል ወሳኝ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡

*(ከዶ.ጋሊ ነጻነትን የማስከበር አኩሪ ታሪክ ገጽ የተወሰደ)*

# አባሪ “ 8 ”

## የማስተማሪያ ጽሑፍ

### አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍን ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚጠቅሙ በተለያዩ ምሁራን የጥናት ዉጤት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ የምሁራን ሀሳብና የማስተማሪያ ዘዴ

አንብቦ መረዳት የተለያዩ ክሂሎች የተዋሀዱበት ሂደት እንደሆነ Ellis and Brain (1980) ይገልጻሉ፡፡ እንደ Grellet (1991) ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መንገዶችን በማመቻቸት የተለያዩ አይነት ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡ ጥያቄዎችም ከምንባቡ አጠቃላይ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ዝርዝርና ግልጽ የተቀመጡ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጥያቄዎቹ አይነትና ተግባርም የተወሰነ ክሂል ከማዳበር ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ለተማሪዎች በሚወጡ ጥያቄዎች አማካኝነት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ጥያቄዎቹ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችንም ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ማንባብና መጻፍ በንባብ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች አብረው ሊያዳብሩት ከሚጠበቅባቸው ክሂሎች ውስጥ አንዱ መጻፍ ነው፡፡

የመጻፍ ክሂል በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት እንዲዳብር ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራትን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፡- **ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣ ሀሳባቸውን ባጭር ባጭሩ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው በተወሰነ መልኩ እንዲያቀርቡ እና አጫጭር ሃሳቦችን አብራርተው በዝርዝር እንዲጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች** የመጻፍ ክሂልን ከንባብ ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲዳብር የሚያግዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

Conley (1997) የማንበብና የመጻፍ ክንዋኔዎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ማንበብና መጻፍ በእለት ተእለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉምን መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝበዋል፡፡ በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ መሆናቸዉን ገልፀዋል፡፡

## 1. አንብቦ የመረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቅሙ ብልሃቶች፡፡

አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ ለአብነት ያህል ጥቂቶችን ለማየት፤

Block (1997) ሲገልጹ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና የመጻፍን ክሂል ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ **ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ መተንበይና መገመት በጥልቀት ማሰብ** የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 1. **ጥያቄ መጠየቅ**

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡

Block (1997) ሲገልጹ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣምረው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው ሲሉ፤ Airasian (1997) በበኩላቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣ በጥልቀት እንዲያነቡና ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Gary (1995) ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድነው? ያወቅኩት ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያሳድግላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡

### 2.**መተንበይና መገመት** (Inferring and predicting)

ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለ ቀጥሎ የሚመጣውን ሁነት ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቁምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው፡፡ መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኝን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ

የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቁምበት ልዩ ስልት ነው::

እንዲሁም Barrs (2000) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንድን ጽሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገጸባህሪያትን ማንነት፣ ድርጊት፣ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ጽሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመጻፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ብልሃቶች አማካኝነት ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ ጥረት የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎቹ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ ትርጉም ይሰጣሉ፣ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ስላነበቡት ወይም ስለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ብልሃት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

### 3.ማጠቃለል (Summarizing)

ማጠቃለልን በሚመለከት Block and Mangeri (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሁፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በዕለት ተዕለት ህይወት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችላቸውን ብልሃቶች መማር ይኖርባቸዋል፡፡

4. **ምሰላ** (Imaging):-

አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ገጸ ባህሪያት፣ ድርጊትና ሁነቶች በአእምሮ ምስል የሚቀረጽበት ስልት ምሰላ ይባላል፡፡ ይህንንም ለአንባቢዎችና ለጸሀፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ በንቃት እንዲያነቡ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ ይህም ብልሃት በህይወት ውስጥ ስሜታዊ ገጠመኞችን ከአመለካከትና ከተጠየቃዊ ገጠመኞች ጋር ለማቀናጀትም ይጠቅማል፡፡ በቋንቋው ሂደት ውስጥ በራሱ ሳይሆን የቋንቋው ሂደት በሚፈጥረው ገጠመኝ ውስጥ ጠልቆ ለመግባት ያስችላል፡፡ ምስል ከሳች ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ እያነበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲናገሩ በማድረግ እያነበቡ እያሉም ምስላቸው እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ በመጠየቅም ማለማመድ እንደሚቻል Block (1997) አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያደራጁ በማድረግ የሚገፉፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ክንዋኔውም ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ መያዝ ሊሆን ይችላል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል፡፡ በመጨረሻም መምህሩ የተማሪዎችን ስራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶች የሚያስፈልጋቸው ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጥያቄዎችም ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቆራኙ የመጻፍ ተግባሮች በጽሁፍ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gary 1995)::

በተጨማሪም ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሲለማመዱ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ ትርጉም እንዲሰጡ፣ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ነገር ማጠቃለያ እንዲሰጡ ማድረግ፣ አንብቦ መረዳትና የጽሁፍ ማቀናበር ችሎታ ማጎልበቻ ብልሃት ተደርጎ ይወሰዳል Gray (1995)፡፡

“የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር በቅንጅት ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ” ለሚል የጥናት ርዕስ ለሚካሄደዉ ሙከራዊ ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ከ10ኛ ክፍል ከተማሪዉ የመማሪያ መጻፍ

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜያት ሰኞና ረቡዕ / በቀን ለ1 ስአት/

የመማሪያ ክፍል የማጠናከሪያ ትምህርት መስጫ

ጠቅላላ የትምህርት ሰዓት፡ 8፡00 ሰዓት

## ትምህርት አንድ

**የትምህርት ርዕስ ፡-** **<u>ቀና አመለካከት</u>**

የትምህርቱ ዓላማ ፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- ✓ ስለ ቀና አመለካከት ጠቀሜታ ተገንዝባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ከተለያዩ ምንጮች የምታገኟቸዉን መረጃዎች በሚመለከት ማስታወሻ ትይዛላችሁ ፡፡
- ✓ አመዛዛኝ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች አንድ ሰዉ ቀና አመለካከት አለዉ ሲባል ምን ማለት ነዉ?
2. ቀና አመለካከት ያላቸዉ ሰዎች በህይወታቸዉ ምን ጠቀሜታ የሚያገኙ ይመስላችኋል? የሌላቸዉስ?
3. በሰዎች ዘንድ ቀና አመለካከት መኖር ሀገራዊ ፋይዳዉ ምንድነዉ?

**ተግባር አንድ፡-** የማንበብ ሂደት

ምንም የማይቻል ነገር የለም!

“ምንም የማይቻል ነገር የለም!”

“ይተዉ እንጂ፣ ዶክተር!” ትሉ ይሆናል፡፡ “እርስዎ የተማሩ ሰዉ ነዎት፡፡”

“እንዴት የማይቻል ነገር የለም!” ይላሉ? “አእምሮዎን ስተዋል እንዴ! ልትሉኝም ትችላላችሁ፡፡”

“አይቻልም!” የሚለዉን ቃል ከአእምሮዬ ዉስጥ ካስወጣሁት ከረምኩ፡፡ ይህ እዉነት ነዉ፡፡ በብዙ ምክንያቶች ከቃሉ ጋር የነበረኝን ቁርጠኝነት አቋርጫለሁ ፡፡

“አይቻልም! የሚለዉ ቃል ብዙዉን ጊዜ በጥቅም ላይ የሚዉለዉ ደንታ ቢስ በሆነ፣ በተስፋ መቁረጥና ፍሬ በሌለዉ ሁኔታ ነዉ፡፡ እና በፍጹም አእምሮዬን አልሳትኩም፡፡ እጄን ለነዚህ ከንቱ ስሜቶች አልሰጥም፡፡ ስለዚህ አይቻልም የሚለዉን ቃል ከስር አዉጥቼ ፈታሁት!”

በምድር ላይ እጅግ አደገኛ አስተሳሰብ የጨለምተኝነት በአስተሳሰብ ነዉ፡፡ ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያለዉ ሰዉ ከዚህ ቀድሞ ተሞክሮ ያልተሳካ አንድ ተግባር የሚያዉቅ ከሆነ ያ ተግባር ያልተሳካዉ መጀመሪያዉኑ የማይቻል ስለሆነ ነዉ፤ ብሎ አምኖ እናንተንም ያሳምኗችኋል፡፡ ዓለም በሙሉ እዉነተኛ ያልሆነች፣ ያልተጨበጠች፣ አስቸጋሪ፣ የማትታሰብ እና የማትቻል እንደሆነች ይሰብካችኋል፡፡ እናም ይህ አይነቱ ሰዉ እድገትን ይገድባል፤ ልማትን ያጨናግፋል፤ ፈጠራን ያቀጭጫል፤ ጠልቆ ማሰብን ይገታል፡፡

**ተግባር ሁለት**

ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ በማድረግ ከላይ ባነበባችኋቸዉ አንቀጾች ዉስጥ ያገኛችኋቸዉን ነጥቦች ለመምህራችሁ ተናገሩ ፤ በሚቀጥሉት የምንባቡ አንቀፆች ዉስጥ ሊነሱ ይችላሉ የሚትሏቸዉን ሐሳቦች ለመምህራሁ ተናገሩ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ቀናዉ አስተሳሰብ የ ይቻላል አስተሳሰብ ነዉ፡፡ የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለዉ ሰዉ አዲስ ሀሳብ ሲያጋጥመዉ የአሸናፊነት ስሜት በዉስጡ ስለሚሰማዉ በገጠመዉ ዕድል የሚደሰት ነዉ፡፡ ለአሮጌ ችግሮች የአዲሱን ትዉልድ መፍትሔዎች በመጠቀም አዲስ ታሪክ ለመስራት ባገኘዉ አጋጣሚ ይነቃቃል፡፡ የማይታለፉ የሚመስሉ እንቅፋቶች የሚፈቱበት አንድ መንገድ አለ ብሎ ስለሚያምንም በልበ ሙሉነት ወደ ተግባር ይገባል፡፡ ሁሌም ለስኬታማ ጉዞዉ ስንቅ የሚያደረገዉ ይቻላል! የሚለዉን ቃል ነዉ፡፡

- የልብ ቀዶ ህክምና ! በፍጹም አይቻልም!
- ሰዉን ጨረቃ ላይ ማስቀመጥ! ተዉ እንጂ! በፍጹም አይቻልም!
- ከአንድ የእግር ኳስ ሜዳ በላይ ቁመት ያለዉ ህንጻ መገንባትና የመሬት መንቀጥቀጥን እንዲቋቋም ማድረግ ! በፍጹም አይቻልም !

አስተዉሉ! እነዚህ ሁሉ ተችለዋል፡፡ አይቻልም ሲሉ የነበሩትም በሀፍረት አንገታቸዉን ደፍተዋል፡፡

እናንተ የዚህ ዘመን ባለአደራዎች፤ ራሳችሁን ከክፉ አስተሳሰብ አርቁ! በቀና አስተሳሰብ አንጹ! ስኬታማ ለመሆን ስንቃችሁ ይቻላል! የሚለዉ ቃል ይሁን፡፡

(ምንጭ፡-ብሮበርት ኤች. ሹለር ተጽፎ በማህሌት ጥላዉን ከተተረጎመዉ አመለካከትን በመለወጥ ሕይወትን መለወጥ የሚያስችሉ ታላላቅ መንገዶች ከሚለዉ መጽሐፍ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ (48-50)፡፡)

**ተግባር ሶስት፡-** በአንብቦ መረዳት የመጻፍ ጥያቄዎች

ትዕዛዝ አንድ ከላይ የቀረበዉን ምንባብ በጥሞና በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ደንታ ቢስ የሆኑ ሰዎች የ“ይቻላል!” መርህ ተከታዮች ያልሆኑበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል? ____________________________________________
2. የጽሁፉ አቅራቢ በዚህ በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ነገር የለም የሚል አቋም አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? ለምን? ምክንያቱን በማስረጃ አስደግፈችሁ ግለጹ!

   ____________________________________________

   ____________________________________________
3. የሚቻሉ ነገሮችን “አይቻልም!” ሲሉ የነበሩ ሁሉ ትንቢታቸዉ ሰምሮላቸዋል ወይስ አለሰመረላቸዉም? ለምን? ምክንያቱን በማስረጃ አስደግፈችሁ ግለጹ!

   ____________________________________________

   ____________________________________________
4. የስኬታማ ህይወት ተቋዳሾች ዓለምን በብሩህ መልኩ የሚቀበሉት ለምን ይመስላችኋል?

   ____________________________________________

   ____________________________________________
5. በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለዉ የሚገባዉ አስተሳሰብ የትኛዉን ነዉ ለምን አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

   ____________________________________________

   ____________________________________________

6. አዲስ ታሪክ ለመሥራት ይነቃቃል፡፡ የተባለዉ ትዉልድ የትኛዉን አስተሳሰብ የሚከተለዉ ነዉ? ለምንስ ስኬታማ ይሆናል ተባለ?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

7. ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያላቸዉ ሰዎች ህይወታቸዉን በምን ዓይነት መንገድ ማስተካከልና መምራት እንዳለባቸዉ ያላችሁን ሀሳብ አብራርታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

**ተግባር አራት ፡ አመዛዛኝ ድርሰት**

የድርሰት ዓይነቶችን በተመለከተ የቋንቋ ሊቃዉንት አንድ አይነት አመለካከት የላቸዉም፡፡ አንዳንዶቹ ስድስት፣ ሌሎች አራት፣ ሌሎች ደግሞ ሶስት ናቸዉ ይላሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የምናየዉ በሁሉም ምድብ ዉስጥ የማይጠፋዉን አመዛዛኝ ድርሰትን ነዉ፡፡

አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚጽፍ፣ የአንባቢዉን (የአድማጩን) የአንድ ጉዳይ እዉነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥር፣ ደራሲዉ(ጸሐፊዉ) ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊጽፍ የሚችልበት፣ ወይም ለሁለቱም አከራካሪ ሐሳቦች የቆመ በመምሰል ጉዳዩን በመደገፍና በመቃወም አቅርቦ በመጨረሻም ማስረጃዉ ያደላመትን አጠናክሮ በመጠቆት አንዱን በማጠናከር ወደ አንድ ዉሳኔ የሚደርስበትና ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት ዓይነት ነዉ፡፡

ትዕዛዝ አንድ፡- ከላይ ስለ አመዛዛኝ ድርሰት ምንነት የቀረበዉን መሰረት በማድረግ ቀና አመለካከት ያላቸዉንና የሌላቸዉን ሰዎች በማነጻጸር ከሁለት ገጽ ባልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

**ክፍል ሁለት የትምህርት ርዕስ:- የአረጋዉያን ሚና**

የትምህርቱ ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- ✓ በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፡፡
- ✓ ስዕላዊ ድርሰት ትጽፉላችሁ፡፡
- ✓ ድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅሶችን በተገቢዉ ቦታ ትጠቀማላችሁ ፡፡

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች፣ አረጋዉያን የሚባሉት የማህበረሰብ ክፍሎች በየትኞቹ የዕድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ የመስላችኋል?
2. አረጋዉያን በማህበረሰቡ ህይወት ዉስጥ ምን ዓይነት የጎላ ተሳትፎ አላቸዉ?

**ተግባር አንድ** ፡-የማንበብ ሂደት

"መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን"

"ዕድሜ መስታወት ነዉ፡፡" ይህ አባባል፣ ሰዎች እድሜያቸዉ እየገፋ ሲሄድ ከህይወት ያካበቱት ልምድና እዉቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነዉ፡፡

አረጋዉያን ከህይወት ብዙ የተማሩ የተማሩ፣ በአያለ የኑሮ ዉጣ ዉረዶች ተፈትነዉ ያለፉ ዕድሜ ባለጸጎች ናቸዉ፡፡ ከህይወት ልምዳቸዉ ጥቂት በጨለፍን ቁጥርም ሚዛን የሚደፋ ቁም ነገር አናጣም፡፡

አረጋዉያን በዕድሜ መግፋት የተነሳ አካላዊ ቅልጥፍናቸዉ እየደከመ ቢሄድም እንኳ አቅማቸዉ በፈቀደዉ መጠን በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተዉ ላናገኛቸዉ እንችላለን፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ዕድሜያቸዉ በማህበረሰቡ ጎልቶ የሚታየዉ የጉልበት ተሳትፏቸዉ ሳይሆን አእምሮአዊ ሀብታቸዉ ነዉ፡፡ አረጋዉያን ታዳጊዎችን ስነ-ምግባር በማስተማርና በመምከር፣ በግለሰብ መካከል ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን በማርገብና በመሸምገል በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ተፈጥሮአዊና ሰዉ ሰራሽ ክስተቶችን ለአዲሱ ትዉልድ በመንገር ታሪክን የማስተላለፍና የመመስከር ከፍተኛ ሚና አላቸዉ፡፡

ተማሪዎች ከላይ ካነበባችኋቸዉ አንቀጾች ምን ተረዳችሁ ?

በተለይ ተከታዩን ትዉልድ ከመምራትና ቀና መስመር ከማስያዝ አኳያ ያላቸዉን ድርሻ ስንመለከት፣ መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን የሚለዉን ብሂል እንድናነሳ ግድ ይለናል፡፡ አረጋዉያኑ የመምከርና የማስተማር ሚናቸዉን የሚጫወቱት በዘዴና በማዋዛት ሲሆን፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃዎችም ዕድሜ ጠገብ የስነ-ቃል ሀብቶቻችን ናቸዉ፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረት፣ ቅኔ፣ ቃላዊ ግጥም፣ እንካ ሰላንቲያ … በሳል ሀሳብ የሚያስተላልፉ ጥበቦች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ስነ-ቃሎች ወጣቶች ወደ ጥፋት እንዳይገቡና አስቀድመዉ እንዲጠነቀቁ ይመክራሉ፡፡ አንዴ የተፈጸመን ጥፋት ማብሰልሰል ዋጋ እንደሌለዉም ይናገራሉ፡፡ የይቅርታ ትልቅነትን ይሰብካሉ፡፡ ጉብዝናን ያበረታታሉ፡፡ ንፉግነትንና ስግበግብነትን ይነቅፋሉ፤ክፋት ምቀኝነትን ይቃወማሉ፡፡

ለምሳሌ የመተባበርን ጠቀሜታ፡- “ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች፡፡” በማለት ለዛ ባለዉ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ “ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል፡፡” በሚል አባባል ችኩልነትን ይቃወማሉ፡፡

በቃላዊ ግጥማቸዉ ጎበዙን፡-

“የበሬዉ ቄስ የበሬዉ መምህር፤

አቆላላፊ ክምር ለክምር፤

ሐምሌ ነሐሴ ያልተራብ ሰዉ፤ ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰዉ፡፡” እያሉ ያሞካሻሉ፡፡

ሰነፉን ደግሞ፡-

“አንድ ወር አይበቃዉም አንድ ወር ያረሰዉ፣

እንኳን ጎተራዉ ቤተሰብ ወቀሰዉ፡፡” በማለት ያንኳስሳሉ፡፡

አረጋዉያን እድሜ አዋቂነትን አጎናጽፏቸዋል፡፡ “አንድ አረጋዊ ሲሞት አንድ ቤተ-መጻሕፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል” የሚባለዉም ለዚሁ ነዉ፡፡ አረጋዉያን ሰናይ ተግባራትን ተመልክተዉ ይመርቃሉ፡፡ እኩይ ተግባራትን ታዝበዉ ያወግዛሉ፡፡ ማህበረሰቡ ይህንኑ በዕድሜና በልምድ ያላቸዉን የመሪነት ብቃት ተቀብሎ ያከብራቸዋል፡፡ “የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ” የሚለዉ አባባል ከላይ ካነሳነዉ አረጋዉያንን ምክርና ቃል ከማክበርና ከመፈጸም ጋር የተቆራኘ ነዉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዜጎች ማህበረሰቡን በመምራትና በመቆጣጠር በኩል ያላቸዉን ሚና ትልቅ ግምት በመስጠት ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግላቸዉ ይገባል፡፡

**ተግባር ሁለት፡- በአንብቦ መረዳት የመጻፍ ጥያቄዎች**

ትዕዛዝ አንድ፡- ከላይ የቀረበዉን ምንባብ በጥሞና በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ማህበረሰባችን ለአረጋዉያን ያለዉ አመለካከት ምን ይመስላል በማስረጃ በማስደገፍ አብራሩ፡፡
2. ስነ-ቃሎች በማህበረሰቡ ዉስጥ ያላቸዉ ፋይዳ ምንድን ነዉ?
3. በወጣቶችና በአረዉያን መካከል ያለዉን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?
4. ከምንባቡ ሐሳብ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋዉያንና ያልተማሩ አረጋዉያን በማህበረሰቡ ያላቸዉ ተቀባይነት እንዴት ዓይነት ይመስላችኋል? በእኩል ዐይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ በማስደገፍ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡
5. በአከባቢያችሁ ያሉ አረጋዉያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸዉን አስተዋጽኦ አስመልክታችሁ ያያችሁን፣ ያነበባችሁን፣ ከሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ አጠናቅራችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**ተግባር ሶስት፡-** ስዕላዊ ድርሰት

ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ምስልና ገጽታ በቃላት አማካይነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር የድርሰት አይነት ነዉ፡፡ በዚህ የድርሰት ዓይነት ደራሲዉ የሚጠቀምባቸዉ ቃላት በሰዉ አእምሮ ዉስጥ ምስል መፍጠር የሚችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

አምሳሉና ደምሴ(1992፡130) ስዕላዊ ድርሰትን ሲገልጹት ‹‹ያንድን ነገር ሁናቴ በዐይን እንዳዩት፣ በእጅ እንደዳሰሱት፣ በጆሮ በቅርብ ሆነዉ እንደሰሙት በጠቅላላዉ ግዙፍ አደርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነዉ፡

**ትዕዛዝ ሁለት፡-** ከላይ ስለ ስዕላዊ ድርሰት ምንነት የቀረበዉን መሠረት በማድረግ የፈለጋችሁትን ርዕስ በመምረጥ ከሁለት ገጽ ያላነሰ አንድ ስዕላዊ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

___

___

___

___

**ክፍል ሶስት**

**የትምህርት ርዕስ፡- ሱስ**

**የትምህርቱ ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-**

- ✓ በተለያዩ የአረፍተ ነገር ስልቶች አረፍተ ነገሮች ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ግጥም ትጽፋላችሁ፡፡

**ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች**

1. ሱስ ምንድን ነዉ?
2. ሰዎች ወደተለያዩ ሱሶች የሚገቡት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
3. በአከባቢያችሁ ሰዎች በብዛት የተጠመዱት በምን ዓይነት ሱስ ነዉ? ምክንያቱስ?

**ተግባርአንድ፡ የማንበብ ሂደት**

**"የጉለሌዉ ሰካራም"**

"በጉለሌ የነበረዉ የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነዉ?" ብለዉ ከገፈርሳ እስከ ደጅአዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች "ተበጀ! ሰካራሙ ተበጀ! ዶሮ ነጋዴዉ ተበጀ!" ብለዉ ይነግሯቸዋል፡፡

የህይወት ታሪክ ፍጹም ገድል ነዉ፡፡ ጢም ያለዉ ሽማግሌ ሰዉ ነዉ፤የራሱን ጸጉር ዉሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያዉቅም፡፡ ማለዳ አይናገርም፤በጠርሙስ የሞላዉን ከጠታ በኋላ ማታ ሲራገም ወይም ሲሳደብ፤ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምጹ ከፈረንጅ ዉሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ ቢያዉቀዉም ባያዉቀዉም ካገኘዉ ጋር ሁሉ ማታ ይስቃል፡፡ የሠላምታዉ ዓይነት እንደወታደር

ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸዉ ነዉ፡፡ ከሠላምታዉ ጋር ድምጽ ትሰማላችሁ ከአፉ የሚወጣዉን አንድ ቃል ግን መለየት አችሉም፡፡

ተማሪዎች  ከላይ ካነበባችሁት አንቀጽ ተበጀ ምን ዓይነት ሰዉ ነዉ? ማህበረሰቡስ ስለእሱ ያለዉ አመለካከት ምን ዓይነት ይመስላችኋል?

ከሚያሰክር ሁሉ ለመታረም ብዙ ጊዜ አስቦ ነበር፡፡ ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ "ከእንግድህ መጠጥ አልቀምስም" እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡ በንጋታዉ የበለጠ ጠጥቶ የባሰ ሰክሯል፡፡ ለመስከር ይጠጣል፤ ደስ ያለዉ እንዲመስለዉ ይጠጣል፤ ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃዉ ሥር መልኩን አይተዉ ያላወቁ ባልቴቶች እንኳ በየፍንጃል ቡናን ፉት እያሉ የሌላዉን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ እያላከኩ ይሳሳቁበት ነበር፡፡

"ይህን መስከርህን ካልተዉክ ላንተ ንሰሐ አባት አልሆንህም" ብለዉ የመጀመሪያ ንስሐ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከእርግማት ጋር አስወግደዉታል፡፡ ሠራተኞቹም ለእርሱ ተቆጥሮ መሥራትን ከዉርደት ቆጥረዉት እየነቀፉት ሄደዋል፡፡ "መጠጥ ካልተዉክ አናገባህም" ብለዉ በየጊዜዉ ለጋብቻ ጠይቋቸዉ የነበሩ በቁመናዉ አስናብተዉታል፡፡ በሰንበቴም፣ በማህበርም ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸዉ ነፍሱን ሳይቀር ንቀዉታል፡፡

ብዙ ጊዜ ሰክሮ አዉቶሞቢል ሄዶበታል፡፡ ሰክሮ በነጋታዉ ሲነቃ እራሱን እስር ቤት ዉስጥ አግኝቷል፡፡ በጉለሌ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የዉሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የጉለሌ ህዝብ አዉጥቶታል፡፡ ሰክሮ የኀርፍ ዉሃ ከወሰደዉ በኋላ ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል፡፡ ሰክሮ ከቤቱ መድረስ እያቃተዉ ከወደቀበት በባቡር መንገድ ሳይነሳ፣ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ኀርፍ ሲሄድበት አድሯል፡፡

ሰዎች መልካም የሰማዕትነት ሥራዉን ሁሉ ርካሽ አድርገዉ ይቆጥሩታል፡፡ በግብረገብ መሠረት አደረግሁት የሚለዉን ሁሉ በስካር እንዳደረገዉ ያናንቁበታል፡፡ "በጎ ሥራዉን ሁሉ በትኩስ መቃብር ዉስጥ አፈር አልብሰዉ፤ አንተ ሰዉ ሰዉ ሁን ሚስት አግባ ልጆች ይኑሩህ" ይሉና ይዘልፉት ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ዉርደትና ርክሰት ነዉ እንጂ ክብር ከቶ አይደለም፡፡ ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰዉ ከሰዉ በታች ነዉ፡፡ ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናዉን አይሹም፡፡ እናም ኑሮዉ በጨለማ እንደተከበበ ይሆናል፡፡ የሰካራሙ ተበጀም ዕጣ ይኸዉ ነበር፡፡

(ተመስገን ገብሬ፣ የጉለሌዉ ሰካራም፣1941፣1-8 ለማስተማሪያ እንዲያመች ተሻሽሎ የቀረበ)

**ተግባር ሁለት** ፡- በአንብቦ መረዳት የመጻፍ ጥያቄ

ትዕዛዝ አንድ፡- ከላይ የቀረበዉን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊትና ካነበባችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ሱስ ምንድነዉ?
2. ሰዎች ወደ ተለያዩ ሱሶች የሚገቡት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
3. ከላይ የቀረበዉን ምንባብ በጥሞና አንብባችሁ እንደተረዳችሁ ተበጀ ምን ዓይነት ሰዉ እንደ ሆነ ፤ ማህበረሰቡ ስለ እሱ ያለዉን አመለካከት ከሶስት አንቀጽ ባለነሰ መልኩ ታሪኩን ጽፋችሁ ለመምህራችሁና ለክፍሉ አቅርቡ፡፡

**ተግባር ሶስት**

1. "ሱስ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳት አለዉ፡፡" የሚለዉን ዓረፍተ ነገር መንደርደሪያ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን አንቀጽ ለጓደኞቻችሁ በማሳየት በሚሰጧችሁ አስተያየት እንደገና አሻሽላችሁ ጻፉ፡፡

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. የሱስን አስከፊ ገጽታን መሰረት ያደረገ በሶስት አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

## ክፍል አራት

**የትምህርት ርዕስ፡- "ሥራና ምርት"**

የትምህርቱ ዓላማ፡- ተማሪዎቹ ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-

- ✓ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ በሠንጠረዥ የቀረበን መረጃ ወደ ዝርዉ ጽሁፍ ትቀይራላችሁ፡፡
- ✓ በዝርዉ የቀረበዉን መረጃ በሠንጠረዥ ታቀርባላችሁ፡፡

<u>ቅድመ ንባብ</u>

1. ሥራና ምርት ያላቸዉ ግንኙነት ምንድነዉ?
2. ጠንክሮ መሥራት ለራስ፣ ለሀገርና ለወገን ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?

ተግባር አንድ፡- የማንበብ ሂደት

**"የሠራ ያገኛል"**

ኢትዮጵያ በርካታ ህጻናትና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣ አከባቢዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊሲ አዉጪዎችና ፖለቲከኞች ሥራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ልጆች ትልልቅ ርዕይና ዓላማ እንዲይዙ በቂ ችሎታና ሙያ እንዲኖራቸዉ ከሁሉም በላይ ወላጆች ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡ በሁሉም መስፈርቶች እያደገ የሚሔድ ቤተሰብ ኃላፊ የሆኑ ወላጆች ያሏቸዉ ልጆች፣ዉስጣቸዉን እየመረመሩ የቤተሰባቸዉን እንቅስቃሴ ወደተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸዉ ምሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች ያሏቸዉ ልጆች ከወላጆቻቸዉ የበለጠ ባለ ራዕይ ይሆናሉ፡፡

ህይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸዉን ሲያስተምሩ፣ በሂደት የእነሱ ህይወት ከዕለት ወደ ዕለት ለዉጥ እያመጣ ሲሄድ፣ በየቤተሰቡ ያለ አንድ ሁለት ሰዉ የራሴ የሚለዉ ሥራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፣ "ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸዉ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸዉ!"

አሁን አሁን እንደሚታየዉ ወላጆች በጣም ዉስን የሆነ ህልምና ራዕይ አላቸዉ፡፡ የሚያጋጥሟቸዉን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላትና ከልጆች መኖር አለመኖር ጋር የሚያያይዙ አሉ፡፡ በመሠረቱ ህጻናት ወላጆቻቸዉን አስገድደዉ የተወለዱ አይደሉም፤ ህጻናትን የምንወልዳቸዉ እኛ ነን፤ በየትኞቹም ኃላፊነቶች በአብዛኛዉ ተጠያቂዎቹ እኛ ወላጆች ነን፡፡ ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የምንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል፡፡ ኢትዮጵያ የምታደርግዉ እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ስደርስ ነዉ፡፡

(ወረታዉ በዛብህ፣ ኢንተርፕሬነርሽፕ፣ 1998፣109፣ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ፡፡)

ተግባር ሁለት፡- በአንብቦ መረዳት የመጻፍ ክሂል ጥያቄዎች

ትዕዛዝ አንድ፡- ከላይ የቀረበዉን ምንባብ በጥሞና በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ከላይ ካነበባችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን በሶስት አንቀጽ ዘርዘር አደርጋችሁ ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ቀና አስተሳሰብ ያላቸዉን ልጆች ለማፍራት የወላጆች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ከላይ በቀረበዉ ምንባብ ተገልጿል፡፡ ይህንን ሐሳብ ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት የራሳችሁን ሀሳብና አስተያየት ከሦስት አንቀጽ ባላነሰ መልኩ ጻፉ፡፡

3. ከዚህ በታች የቀረቡላችሁን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ‹‹ሥራና ምርትን›› በተመለከተ ሁለት አንቀጽ ጻፉ፡፡

ስለዚህ፣ ይሁን እንጂ፣ ነገር ግን፣ በመሆኑም፣ ወይም፣ ለምሳሌ፣ እና፣ በአንጻሩ፣ ደግሞ

4. በሠንጠረዥ የቀረበላችሁን መረጃ መሠረት በማድረግ ርዕስ ሰጥታችሁ አንድ አጭር ጽሁፍ ጻፉ፡፡

| ገበሬዉን እርሻ ለማረስ ያነሳሱት ምክንያቶች | ያከናወናቸዉ ተግባራት በቅድመ ተከተል | ያመረተዉ ምርት | ያመረተዉን ምርት እንዴት ተጠቀመበት |
|---|---|---|---|
| ✓ ራሱንና ቤተሰቡን(3 ልጆቹን በበቂ ሁኔታ ለመመገብ<br>✓ ልብስ ለመግዛት<br>✓ የፋብሪካ | ✓ የእርሻ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት(ጅራፍ፣ ሞፈር፣ወገል፣ ቀንበር፣ ማረሻ፣ ድግር፣ ምራን…..)<br>✓ ሦስት እያስተጋገዘ | ✓ ሦስት ጎታ ጤፍ<br>✓ ሁለት ጎታ ዳጉሳ<br>✓ አንድ ጎስጎሽ በርበሬ<br>✓ አንድ ይዘቱ 60ሜ$^3$ የሆነ | ✓ ልጆቹን፣ ሚስቱንና ራሱን በሚገባ መገበ<br>✓ ለት/ቤት የሚሆኑ መሣሪያዎቻቸ ዉን ለልጆቹ አሟላ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዉጤቶች (እንደዘይት፣ ጨዉ፣ ሳሙና….. ያሉትን ለመግዛት ለመጠቀም<br>✓ ልጆችን ት/ቤት ሰዶ ለማስተማር<br>✓ ሌሎች ፍላጎቶችን ለማሟላት | የሚጠምዳቸዉ በሬዎች መግዛት<br>✓ ለመቆጥቆጫና ለመጥረብ የሚያገለግል መጥረቢያ (ምሳር)መግዛትና እጀታ ማበጀት<br>✓ የበሬዎች ማደሪያና የሥራ ዕቃዎች ማዘጋጀት | ጎተራ ሙሉ በቆሎ ወዘተ.. | ✓ ቆርቆሮ ቤት ሠራ |
| | ✓ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ በቆሎ(ማሽላ)፣ አተር፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ ወዘተ… ወቅታቸዉን ጠብቆ መዝራትና ማረም፡፡ ወዘተ… | | ✓ ለመጓጓዣና ለመጓጓዝ የሚሆኑ አንድ የበቅሎና አንድ አህያ ገዛ ወዘተ… |

**<u>የንግድ የሥራ ደብዳቤ</u>**

የሥራ ደብዳቤዎች በዋናነት  በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም የድርጅት ወይም የመሥሪያ ቤት የሥራ ደብዳቤ እና የግል ደብዳቤ የሚባሉት ናቸዉ፡፡

የንግድ ስራ ደብዳቤ ከድርጅት ወይም ከመ/ቤት የሥራ ደብዳቤ የሚመደብ ሲሆን አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የንግድ ሥራን (ሽያጭን፣ ግዢና ልዉዉጥን) አስመልክቶ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚጻፈዉ ደብዳቤ ነዉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ደብዳቤ የዕቃዎችን ዋጋ ለመጠየቅ፣ ለዋጋ መጠየቂያ ደብዳቤ ምላሽ ለመስጠት ስሞታ  ካለ ለመሰንዘር፣ ለቀረበዉ የግዢ ጥያቄ ፈጣንና አርኪ ምላሽ ከተገኘ ምስጋና ለማቅረብ ወዘተ የሚጻፍ ነዉ፡፡

ቁጥር፡- -----------

ቀን፡- --------

| የራስጌ ማህተብ |
|---|

ለ ______________________________

(ከተማ፣)

ጉዳዩ ፡- ______________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________::

የግርጌ ማተብ

ከሠላምታ ጋር!

ፊርማ_______________

ሙሉ ስም (ኃላፊነት)

ግልባጭ፡-______________________

5. ከላይ የቀረበዉን የንግድ ሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ መመሪያን እና የንግድ ሥራ ናሙና በመከተል በመረጣችሁበት ርዕሰ ጉዳይና አድራሻ አንድ የንግድ ሥራ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

6. ከሰዎች ጠይቃችሁም ይሁን መጻሕፍት አንብባችሁ በንግድ ሥራ ዉስጥ አንድ ድርጅት እንዲቀጥራችሁ የቅጥር ማመልከቻ ደብዳቤ ጽፋችሁ ለመምህራሁ አቅርቡ፡፡

# አባሪ “ 9 ”

## በጥናቱ የተከናወኑ ተግባራት

ጥናቱ የተጀመረዉ በሚያዚያ 4 /08/ 2013 ዓ.ም ሲሆን በኮቪድ-19 ምክንያት በ16 የመማሪያ ክፍሎች ተመድበዉ የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን አራት ክፍሎችን በቀላል የዕጣ ናሙና በመጠቀም አራት የአስረኛ ክፍል ደረጃ የሚማሩ 120 ተማሪዎችን የጥናቱ አካላይ ለማድረግ ቢፈለግም የተማሪዎች የችሎታ ደረጃ መታወቅ የግድ ስለነበር የቅድመ ትምህርት ፈተና መስጠት አስፈለገ፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ በናሙነት ለተመረጡ 120 ተማሪዎች የችሎታ ስብጥራቸዉን ለማወቅ የቅድመ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተና ከተፈተኑ ከ120 ተማሪዎች ተቀራራቢ ዉጤት ያስመዘገቡትን 50 ተማሪዎችን በመለየት በሁለት ቡድን በመክፈል 25 ተማሪዎችን ለሙከራ 25 ተማሪዎችን ደግሞ ለቁጥጥር ቡድን ዉለዋል፡፡

**ሳምንት አንድ**

በሳምንት አንድ ሚያዚያ 25/08/2013 ዓ.ም የሙከራ ትምህርት ለመስጠት ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በመያዝ ትምህርቱን መስጠት ተጀመረ፡፡

በትምህርቱ መግቢያ ተማሪዎች፡-

- ✓ አንብቦ መረዳት ማለት ምን ማለት ነዉ?
- ✓ መጻፍ ማለትስ ምን ማለት ነዉ ?

የሚሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ትምህርቱ ተጀመረ ተማሪዎችም እጃቸውን በማንሳት ይሆናል ያሉትን መልስ እንዲመልሱ አደረኩ፡፡ ከመልሶቻቸው መካከል አንብቦ መረዳት ማለት አንድበጽሁፍ የቀረበን ሀሳብ መረዳት ማለት ነዉ፡፡ መጻፍ ማለት አንብበን የተረዳነዉን መጻፍ ነዉ ብለዉ መልሰዋል፡፡ እኔም ተማሪዎቹ የመለሱትን መልስ በመቀበል በመማሪያ መጻፋቸዉ በገጽ 66 ላይ ቀና አመለካከት በሚል ርዕስ የቀረበዉን ምንባብ እንዲያነቡ ትዕዛዝ ሰጥቼ ምንባቡን ከማንበባቸዉ በፊት ተማሪዎቹን ቅድመ ንባብ ጥያቄ ጠይቄያቸዋለሁ፡፡ ጥያቄዉም

ተማሪዎች ፡-

1. አንድ ሰዉ ቀና አመለካከት አለዉ ሲባል ምን ማለት ነዉ?
2. ቀና አመለካከት ያላቸዉ ሰዎች በህይወታቸዉ ምን ጠቀሜታ የሚያገኙ ይመስላችኋል? የሌላቸዉስ? የሚል ነበር፡፡

ከጥያቄዎቹ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ አደረኩ፡፡ ምንባቡን እያነበቡ ሶስተኛ አንቀጽ ላይ በማስቆም ፤

**ጊዜ ምንባብ ጥያቄ አቀረብኩላቸዉ፡፡**

**ጥያቄዎቹም፡-**

- ተማሪዎች ከመጀመሪያዎቹ ሶስት አንቀጾች ምን ተረዳችሁ የተረደችሁትን በደብተራችሁ ላይ አስፍሩ፡፡
- ቀጥሎ የሚመጣዉስ ሀሳብ ምን ይመስላኋል ግምታቸዉን በደብተራቸዉ ላይ እንዲጽፉ

በማድረግ፤ ቀሪዉን የምንባቡን ክፍል አንብበዉ እንደጨርሱ በደብተራቸዉ ላይ ያሰፈሩትን ግምታዊ ሀሳብ ምንባቡን አንብበዉ ከጨረሱት ሀሳብ ጋር መመሳሰሉንና ግምታቸዉ ልክ መሆን አለመሆናቸዉ እንዲያረጋግጡ በማድረግ ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡትን መልመጃዎች እንዲሠሩ በማድረግ የዕለቱ የትምህርት ሠዓት ተጠናቀቀ፡፡

<u>የቤት ሥራ</u>

<u>የቀረበላችሁን ምንባብ በጥሞና በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡</u>

8. ደንታ ቢስ የሆኑ ሰዎች የ"ይቻላል!" መርህ ተከታዮች ያልሆኑበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

_______________________________________________

9. የጽሁፉ አቅራቢ በዚህ በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ነገር የለም የሚል አቋም አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? ለምን? ምክንያቱን በማስረጃ አስደግፈችሁ ግለጹ!

_______________________________________________

_______________________________________________

10. የሚቻሉ ነገሮችን "አይቻልም!" ሲሉ የነበሩ ሁሉ ትንቢታቸዉ ሰምሮላቸዋል ወይስ አለሰመረላቸዉም? ለምን? ምክንያቱን በማስረጃ አስደግፈችሁ ግለጹ!

_______________________________________________

_______________________________________________

11. የስኬታማ ህይወት ተቋዳሾች ዓለምን በብሩህ መልኩ የሚቀበሉት ለምን ይመስላችኋል?

_______________________________________________

_______________________________________________

12. በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለዉ የሚገባዉ አስተሳሰብ የትኛዉን ነዉ ለምን አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

________________________________________________________________

______________________________________________________

13. አዲስ ታሪክ ለመሥራት ይነቃቃል፡፡ የተባለዉ ትዉልድ የትኛዉን አስተሳሰብ የሚከተለዉ ነዉ? ለምንስ ስኬታማ ይሆናል ተባለ?

________________________________________________________________

______________________________________________________

14. ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያላቸዉ ሰዎች ህይወታቸዉን በምን ዓይነት መንገድ ማስተካከልና መምራት እንዳለባቸዉ ያላችሁን ሀሳብ አብራርታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________

## ሳምንት አንድ

### ክፍለ ጊዜ ሁለት

**ቀን** 27/ 8/ 2013 **ዓ.ም.**

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደተማሩና ምን ምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ፤ የተሰጣቸዉን የቤት ሥራ መሥራታቸዉን በመመልከት በጋራ እርማት በመስጠት ወደ ዕለቱ የትምህርት ርዕስ ተገብቷል፡፡ የዕለቱ የትምህርት ርዕስ አመዛዣኝ ድርሰት የሚል ሲሆን በቅድመ ትምህርት ተማሪዎቹን ስለ ድርሰት ምንነትና ስለ ድርሰት አይነቶች ተጠይቀዉ ወደ አመዛዣኝ ድርሰት ምንነት ገለጻና ማብራሪያ ተሰጥቷቸዉ በክፍለ ጊዜ አንድ ያነበቡትን ምንባብ ዳግም እንዲያነቡት በማድረግ በአጻጻፍ ስልቱ በቂ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በመጨረሻም በአመዛዣኝ ድርሰት **ቀና አመለካከት ያላቸዉ ሰዎችና ቀና አመለካከት የሌላቸዉ ሰዎች በሚል ርዕስ** በማነጻጸር በሶስት አንቀጽ የሚጻፍ የክፍል ሥራ በመስጠት የዕለቱ ትምህርት ተጠናቋል፡፡

**ሳምንት ሁለት**

**ክፍለ ጊዜ ሶስት**

02/09/2013 ዓ.ም

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደተማሩና ምን ምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ፤ ወደ ዕለቱ የትምህርት ርዕስ ተገብቷል፡፡ የእለቱ የትምህርት ርዕስ፡- የአረጋዊያን ሚና በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ሲሆን ምንባቡን ከማንበባቸዉ በፊት በቅድመ ምንባብ ጥያቄ ተማሪዎቹን አረጋዊያን የሚባሉት እነ ማናቸዉ በስንት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ናቸዉ በማለት በመጠየቅ ወደ ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ተደርጓል፡፡ በማስከተለም ምንባቡን እያነበቡ እያለ በማስቆም ያነበቡትን የመጀመሪያዎቹን አንቀጽ ሀሳብ በአንድ አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ በማድረግ የሚቀጥለዉን የአንቀጽ ሀሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታቸዉን እንዲያሰፍሩ በማድረግ ቀሪዉን የምንባቡን ክፍል አንብበዉ እንዲጨርሱ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ በሁለት አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ዉስጥ ለጓደኞቻቸዉና ለኔ እንዲያነቡልኝ በማድረግ ጥሩ አሳጥረዉ ለጻፉት ተማሪዎች እንደ አጻጻፋቸዉ የተወሰነ ማርክ በመያዝ የዕለቱ የትምህርት ርዕስ የተቋጨ ቢሆንም በየቤት ስራ መልክ የተወሰኑ መልመጃዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

**መልመጃዎቹም ከምንባቡ የወጡ ሲሆን እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡**

6. ማህበረሰባችን ለአረጋዉያን ያለዉ አመለካከት ምን ይመስላል በማስረጃ በማስደገፍ አብራሩ፡፡
7. ስነ-ቃሎች በማህበረሰቡ ዉስጥ ያላቸዉ ፋይዳ ምንድን ነዉ?
8. በወጣቶችና በአረዉያን መካከል ያለዉን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?
9. ከምንባቡ ሐሳብ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋዉያንና ያልተማሩ አረጋዉያን በማህበረሰቡ ያላቸዉ ተቀባይነት እንዴት ዓይነት ይመስላችኋል? በእኩል ዐይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ በማስደገፍ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡
10. በአከባቢያችሁያሉ አረጋዉያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸዉን አስተዋጽኦ አስመልክታችሁ ያያችሁን፣ ያነበባችሁን፣ ከሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ አጠናቅራችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ የሚሉ ናቸዉ፡፡

ሳምንት ሁለት

ክፍለ ጊዜ አራት

04/09/2013 ዓ.ም

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደተማሩና ምንምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ፣ የተሰጣቸዉን የቤት ሥራ መሥራታቸዉን በመመልከት በጋራ እርማት በመስጠት ወደ ዕለቱ የትምህርት ርዕስ ተገብቷል፡፡ የዕለቱ የትምህርት ርዕስ ፡- ስዕላዊ ድርሰት የሚል ሲሆን ስለ ስዕላዊ ድርሰት ምንነት በጥያቄ መልክ ተማሪዎቹን በመጠየቅ ስለ ስዕላዊ ድርሰት አጭር ማስታወሻና ገለጻ በማድረግ በተጨማሪም የአረጋዊያ ሚና የሚለዉን ምንባብ ዳግም እንዲያነቡ በማድረግና የተጻፈበትን የአጻጻፍ ስልት በመጠየቅ፣ በፈለጉት ርዕስ ቤታቸዉ ሄደዉ በሶስት አንቀጽ የሚጻፍ ስእላዊ ድርሰት ጽፈዉ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያነቡላቸዉ በመንገር የዕለቱ የትምህርት ርዕስ ተቋጭቷል፡፡

ሳምንት ሶስት

ክፍለ ጊዜ አምስት

09/09/2013 ዓ.ም

የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ያለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምን እንደተማሩና ምን ምን ተግባራትን እንዳከናወኑ በመጠየቅ፣ በስዕላዊ ድርሰት ጽፈዉ እንዲመጡ የተሰጣቸዉን የቤት ሥራ በመመልከት ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያነቡ በማድረግና በጻፉት ድርሰት ዙሪያ በጋራ በመነጋገር እርማት በመስጠት እንደገና አስተካክለዉ እንዲጽፉ በማደርግ የዕለቱ የትምህርትርዕስ ተቋጭቷል፡፡

ሳምንት ሶስት

ክፍለ ጊዜ ስድስት

11/09/2013 ዓ.ም

የዕለቱ የምንባብ ርዕስ፡ - ሱስ በሚል የቀረበ ምንባብ ሲሆን ተማሪዎቹ ወደ ምንባቡን ከማንበባቸዉ በፊት ስለ ሱስ ምንነትና ሰዎች ወደ ተለያዩ የሱስ አይነቶች በምን ምክንያት እንደሚገቡ በመጠየቅ ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ተደርገዋል፡፡ በማስከተለም ተማሪዎቹ ምንባቡን እያነበቡ በምናባቸዉ ምን ምን እንደሚከሰትና እንደሚመላለስ በመጠየቅ በምናባቸዉ የሚታያቸዉን ነገር በደብተራቸዉ ላይ ማስታወሻ እየያዙ ምንባቡን አንብበዉ እንዲጨርሱ ተደጓል፡፡
በማስከተልም አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ በአንድ አንቀጽ አሳጥረዉ ጽፈዉ በክፍል ዉስጥ እንዲያነቡ ተደርጓል፡፡

## ሳምንት አራት

## ክፍለ ጊዜ ሰባት

## 23/09/2013 ዓ.ም

ለዕለቱ ትምህርት የቀረበዉ የምንባብ ርዕስ ፡- ሥራና ምርት በሚል የቀረበ ምንባብ ሲሆን ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ በማድረግ አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ ቅድመ ተከተሉን በጠበቀ መልኩ በሁለት አንቀጽ አሳጥረዉ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

በማስከተልም ምንባቡን መሠረት ያደረገ የተለያዩ መልመጃዎች ተሰጥቷቸዉ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ከሚያዚያ 25/ 8/ 2013 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 25/ 9/ 2013 ዓ.ም. ለአራት ሳምንታት የተከናወነው የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ምንባብ እያነበቡ የሚቀጥለዉን የምንባብ ክፍል እንድገምቱ የሚያደርግ፤ ምንባቡን ለምንድነዉ የማነበዉ ብለዉ ራሳቸዉን እንዲጠይቁ የሚያደርግ፤ ምንባቡ የተደራጀበትን የአጻጻፍ ስልት እንዲለዩ በአንድ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲለዩ አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚያስችሉ ነበሩ፡፡ በቀጣይ የተከናወነው ተግባር ድህረ ትምህርት ፈተናውን መፈተን ነው፡፡ የፈተናው ጥያቄዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ተመሳሳይ እንዲሆኑ በማድረግ ተዘጋጅተው ግንቦት 30/ 9/ 2013 ዓ.ም. ተሰጥቷቸዋል

## ማረጋገጫ

"የአንብቦ መረዳትን ክሂል ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መዳበር ያለዉ ዉጤታማነት ፍተሻ" (በሰኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም <u>ታረቀኝ አይሶ</u>

ፊርማ -------------------

ቀን ---------------------